## ዋና ጭብጥ ፡

# ክርስቶስን ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ መስበክ

## ሞጁል፡ አንድ

## 1. ክርስቶስና ቅዱሳት መጻሕፍት

“ክርስቶስን ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ መስበክ” በሚል ርዕስ ላይ እንድናገር ተጋብዣለሁ። ምናልባት ይህ ጉዳይ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ሙሉ ለሙሉ የሚያያዝ እንደሚሆን ታስቡ ይሆናል፣ ምክንያቱም ከምንም ነገር በላይ ክርስቶስን ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የመስበክ ችግር ስለሌለብን ነው። እያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን ስብከት ስለ ክርስቶስ የሚናገር መሆን አለበት፤ ትክክል ነኝ?

ነገር ግን ይህ ፈጽሞ ላይሆን ይችላል። ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ክርስቶስ የምንሰብከው ብዙ ነገር ይኖራል፣ ደግሞም አዲስ ኪዳንን እየሰበኩ ክርስቶስን አለመስበክም በጣም ይቻላል። ስለ ክርስቶስ ብዙ ተናግረህ ስሙንም ብዙ ጊዜ ደጋግመህ ጠቅሰህ፣ ነገር ግን እርሱን መስበክ ላይ ተሳስተህ ይሆናል። ለምሳሌ “ኢየሱስ መልካምን እያደረገ ሄደ፣ ስለዚህ እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን” በሚለው ስብከትህ ውስጥ የሥነ-ምግባር ትምህርትን ባልጠበቅከው ሁኔታ አስተምረህ ይሆናል - ወይም ደግሞ ስብከትህ ታላቁን በእምነት የመጽደቅ አስተምህሮን በግልጽ የሚናገር ሊሆን ይችላል። ይህን ማድረግህ በራሱ መጥፎ ትምህርት ወይንም የማይጠቅም አይደለም፣ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ክርስቶስን አይሰብኩም።

ስለዚህ ክርስቶስን ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ መስበክ ምን ማለት እንደሆነ ማየት ያስፈልገናል። ነገር ግን አስቀድመን “ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል” ስንል ምን ማለት እንደሆነ ማየት አለብን። ምክንያቱም ክርስቶስን ከሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ለመስበክ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አንዳንድ ነገሮችን መረዳት ይገባናል።

*መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ደራሲ ያለው፣ አንድ መጽሐፍ ነው*

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ደራሲዎች ከተጻፉ 66 መፃሕፍት የተጠናቀረ ሲሆን፣ አንዳንዶቹን ደራሲዎች እናውቃቸዋለን፣ አንዳንዶቹን አናውቃቸውም። የዳዊትን መዝሙር ሆነ ወይም የጳውሎስን ደብዳቤዎች ስንመለከት

እነዚህ ሁሉ ደራሲያን የተለያየ ተፈጥሮና ሰብእና ያላቸው መሆናቸውን በጽሑፋቸው ውስጥ ማየት እንችላለን። ሆኖም ግን ከእነዚህ ሁሉ ደራስያን በስተጀርባ አንድ ደራሲ አለ። ጳውሎስ ሲጽፍ “ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ
የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው” ይላል (2ጢሞ. 3፡16)። ጀምስ ኢነል ፓከር ሲናገር አንድ ዋና ገጸ-ባህርይ አለ(ፈጣሪ እግዚአብሔር) ነው፣ አንድ የታቀደ ታሪክ አለ (የዓለም ሕዝብ መቤዠት) ነው፣ አንድ ደግሞ የትኩረት ማዕከል አለ (የእግዚአብሔር ልጅና አዳኝ የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ) ነው፣ ደግሞም የእግዚአብሔርን ማንነት እና እግዚአብሔርን መምሰልን የሚያዋህድ አንድ የአስተምህሮ ክፍል አለ። “በእውነትም የመጽሐፍ ቅዱስ ውስጣዊ ስምምነት(አንድነት) ተአምራዊ ነው፣ ምልክትና ድንቅም ነው፣ የእኛን ዘመን አለማመንም የሚሞግት ነገር ነው”።

በተለይ “የትኩረት ማዕከል” ወደሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሰን እንመጣለን፣ በርግጥም እርሱ የሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ትልቁ ጭብጥ ነው ማለት እንችላለን። ሆኖም ግን አስቀድመን መጽሐፍ ቅዱስን እንደ አንድ መጽሐፍ መገንዘባችንን ርግጠኞች እንሁን። መጽሐፍ ቅዱስን በብዙ ምዕት-ዓመታት ውስጥ የተጻፈ እና በአንድ ወቅት ወደ አንድ ጥራዝ የተሰበሰበ የመጻሕፍት ስብስብ አድርጋችሁ ካሰባችሁ፣ ክርስቶስን ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ መስበክ አትችሉም። መልእክቶቹን ከዚህም ከዚያም ትሰብኩ ይሆናል፣ እንዲኹም ከክርስቶስ ጋር በኾነ መንገድ ታገናኟቸው ይሆናል፣ ነገር ግን ትክክለኛ የሆነ ግንኙነትን በመጻሕፍት ውስጥ አታዩም። ጥሩ የሆኑ ክርስቲያኖች መጥፎ ስብከት ሊሰብኩ ይችላሉ። ለዚህም ነው እንደ ሰባኪያን የተወሰነ ሥልጠና ልንወስድና መጽሐፍ ቅዱስን በተሻለ ሁኔታ ልንረዳ የሚገባን። ከቃሉ ውስጥ ክርስቶስን ሳንገልጥና ሳናሳይ፣ ሃይማኖታዊ የሆኑና እጅግ ልብን የሚያሞቁ ትምህርቶችን እንሰብክ ይሆናል። ወይም ደግሞ ክርስቶስን ሳንሰብክ፣ ሰዎች እንዴት ዓይነት ባህርይ ማሳየት እንዳለባቸው የሞራል ትምህርቶችን እንሰብክ ይሆናል፤ ይህንም እንደምናደርግ እገምታለሁ። ወንጌልን እየሰበክን እንኳ፣ ከፊታችን ካለው ጽሑፍ በትክክልለኛ መንገድ እንደማንሰብክ እገምታለሁ።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የጸና እምነት ያስፈልገናል፣ ደግሞም ቆም ብለን ስለ “እግዚአብሔር ቃል” እና ስለ “እስትንፋሰ እግዚአብሔር” ምንነት ካሰብን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ተጠብቆ የቆየ አንድ መጽሐፍ እንደሆነ እንገነዘባለን፤ ስለዚህም መልእክቱ አንድ ነው፣ ደግሞም በውስጡ ያሉት የተለያዩ ይዘቶች አንድ ወጥ የሆነ ምልዐትን ይመሠርታሉ።

ክርስቶስ የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ጭብጥ ነው

ይህ እውነት መሆኑን ማሳየት ያስፈልገኝ ይሆን? በብሉይ ኪዳን ኢየሱስ ተተንብዮአል፣ በወንጌል ኢየሱስ ተገልጧል፣ በሐዋርያት ሥራ ኢየሱስ ተሰብኳል፣ በመልእክታት ኢየሱስ ተብራርቷል፣ በዮሐንስ ራዕይ ኢየሱስ ዳግም እንደሚመጣ ይጠበቃል (J.A. Motyer, *Look to the* Rock, IVP 1996, p 22)። ሉዊስ በርክሆፍ ይህንን አስረግጦ ሲናገር፣ “የቅዱሳት መጻሕፍት ትረካዎች ማብራሪያን የሚያገኙት አንድ ላይ አብሮ በሚያስሩቸው ማዕከል ብቻ ሲሆን፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (Principles of Biblical Interpretation, Baker 1950, p 142)። ይህን በተመለከተ ቅን የሆኑ ሰዎች ምላሽ ሲሰጡ “በእርግጥም ትክክል ነው” እንደሚሉ አውቃለሁ፣ ነገር ግን ወደ ስብከት ሲመጣ፣ ክርስቶስ በሚገርም ሁኔታ የለም፣ ወይም ደግሞ ክርስቶስ ስብከት ውስጥ እያለ በዛባ ሁኔታ ተሰብኳል፣ ወይም በስብከታቸው ውስጥ ተሰውሯል። ከዚህ በፊት ክርስቶስ የሚገባውን ያህል ያልተገኘባቸውን ብዙ ስብከቶችን እንደሰበክሁ አምናለሁ። ሁልጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናገራለሁ፣ ክርስቶስም ዋናው ምስልና ጭብጥ እንደሆነ አውቃለሁ፣ ነገር ግን እንደሚገባኝ መጠን እርሱን እየሰበኩት አይደለም። ይህ አስቸጋሪ የሆነበት አንዱ ምክንያት በሰይጣን ተንኮል ሲሆን፣ እኛን ለማደናቀፍና ክርስቶስን ለማጨለው የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ሆኖም ግን ሰይጣንን ልወቅስ አልችልም! የእግዚአብሔር ቃል አለን፣ መንፈስ ቅዱስ አለን፣ ጸሎት አለን እንዲሁም አእምሮ አለን - በተሻለ ሁኔታ መስበክ አለብን።

እንዴት መስበክ እንዳለብን ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳየናል

ከመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቶስን ለመስበክ ሥልጣንን የምናገኘው ከየት ነው? ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በኤማሁስ መንገድ በሳምንቱም የመጀመሪያ ቀን፣ ከስቅለቱም በሦስተኛው ቀን፣ ጌታ ተስፋ ወደቆረጡት ሁለት ደቀ መዛሙርት ቀረበ። ስለ ተከሰቱት ነገሮች ይነጋገሩ ነበር። በእርጋታ ገሰጻቸው፣ ከዚያስ

ስለ ስቅለቱና ትንሣኤው ለእነርሱ ለማብራራት ምን አደረገ? "ተመልከቱ፣ እኔ ነኝ!" ማለት ይችል ነበር። ወይም አዲስ ኪዳንን ወይንም የአዲስ ኪዳንን የተወሰኑትን ክፍሎች ሊሰጣቸው ይችል ነበር። በመሰረቱ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ዘላለማዊ ቃል - የቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ መገኛ ነው። ሆኖም ግን ነባር ወደሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ወይንም ብሉይ ኪዳን ብለን ወደምንጠራው በመዞር፣ "እናንተ የማታስተውሉ ሰዎች፣ ልባችሁም ነቢያት የተናገሩትን ሁሉ ከማመን የዘገየ፣ ክርስቶስ ይህን መከራ መቀበልና ወደ ክብሩም መግባት አይገባውምን?" ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን አስረዳቸው" (ሉቃ. 24፡25-27፤ ቁ. 44፤ ሐዋ. 1፡1-3)።

ኢየሱስ የተናገረው ነገር (1). በእነዚህ ጽሑፎች ውስጥ ሁሉ እንደሚኝ ነው፣ (2). እርሱን የሚመለከቱ ነገሮችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ "ልንተረጉም" (በግልጽ ልናብራራ) ይገባናል፣ (3). ስለ እርሱ እውነትን ለማግኘት ከቅዱሳት መጽሓፍት ልንጀምር ይገባናል፣ እርሱም በዚህ መንገድ ለቤተክርስቲያንና ለትውልድ ሁሉ ሥልጣንን አስቀምጧል፣ (4). የሞቱንና የትንሣኤውን ትርጉም ለማስረዳት ቅድሚያ እንሰጣለን - ይህም የወንጌል ዋና ማዕከል ነው፤ "ክርስቶስ ይህን መከራ ሊቀበል . . . እንዲሁም ወደ ክብሩም መግባት ይገባዋል"። ኢየሱስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ናዝሬት በሚገኘው ምኩራብ ከቅዱሳት መጻሕፍት ስለራሱ ጠቅሶ ተናግሮ ነበር - ሉቃ 4፡17-21።

17 የነቢዩ ኢሳይያስ ጥቅልል መጽሐፍም ተሰጠው፤ ጥቅልሉንም መጽሐፍ በተረተረው ጊዜ እንዲህ ተብሎ
የተጻፈበትን ክፍል አገኘ፤ 18 "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣ እርሱ
ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩት መፈታትን፣
ለታወሩትም ማየትን እንዳውጅ፣ የተጨቈኑትን ነጻ እንዳወጣ፣ 19 የተወደደችውንም የጌታን ዓመት
እንዳውጅ ልኮኛል።" 20 ከዚያም መጽሐፉን ጠቅልሎ ለአገልጋዩ መልሶ ሰጠውና ተቀመጠ፤ በምኵራብ
የነበሩትም ሁሉ ትኵር ብለው ይመለከቱ ነበር። 21እርሱም፣ "ይህ በጆሮአችሁ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል
ዛሬ ተፈጸመ" ይላቸው ጀመር።

ኢየሱስ ስለራሱ ከብሉይ ኪዳን አስተምሯል። የሚወደው መጠሪያው "የሰው ልጅ" የሚለው ሲሆን፣ ይህም ስያሜ በዋናነት የመጣው ከዳን. 7፡13 ነው - ሰማያዊና ከፍ ያለ ሆኖ ነገር ግን የሰው አምሳል ሆኖ ከጥንት በፊት ታላቅነትና አምልኮን ለመቀበል መጥቷል (ማቴ. 8፡20፤ 20፡23፤ 11፤18፤ ማር. 14፡62፤ ሉቃ. 9፡21፤ 19፤10 ይመልከቱ)። ኢየሱስ በኢሳያስ የተጻፈውን አገልጋይ እንደሚፈጽም አስተምሯል (ማቴ. 12፡15-21)። ኢየሱስ ከዮናስ ይበልጣል (ማቴ. 12፡41)፣ እንዲሁም ከሰለሞን ይበልጣል (12፡42)። እርሱ ከቤተ መቅደሱ ይበልጣል (ማቴ. 12፡6፤ ዮሐ. 2፡19 ይመልከቱ)፤ እንዲሁም ከሙሴ ይበልጣል (ዮሐ. 6፡32፤33)። ከብዙ ዓመታት በኋላ የወንጌል ጸሐፊዎች ወንጌልን ሲጽፉ፣ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ተስፋዎችና ትንቢቶች ፍጻሜ እንደሆነ በሚገባ አውቀው ነበር። ስለዚህም ለምሳሌ በማቴዎስ ወንጌል ከአብርሃም እስከ ኢየሱስ ድረስ ያለውን የዘር ሐረግ እንመለከታለን (1፡1-17)፤ ወይም በሉቃስ ከኢየሱስ ወደ አዳም ያለውን ወደ ኋላ እንመለከታለን (ሉቃ. 3፡23-38)፤ በተደጋጋሚ የተጻፈ ሐረግ አለ "እንዲህ ተብሎ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆነ . . ." (ማቴ. 1፡22፤ 2፡15፤
4፡14-17)። መጥምቁ ዮሐንስም ኢየሱስን የተስፋ ቃል የተነገረለት አድርጎ ይቆጥረዋል (ማቴ. 3፡3)።

ዮሐንስ በወንጌሉ፣ በተለይም ደግሞ በኢየሱስ የምድር ሕይወት መጨረሻ ላይ፣ የተፈጸሙ ትንቢቶችን ያመለክታል (ዮሐ. 13፡18፤ 19፡24፣ 28፤ 36)። እነዚህ ነገሮች በቀጥታ ቃል በቃል ስንረዳቸው በብዛት ትንቢቶች አልነበሩም፤ አንዳንዶቹ መዝሙሮች ነበሩ፣ ለምሳሌ አንድ ታሪካዊ ገጸ-ባህሪን ወይንም ሁናቴ በመጥቀስ የወንጌል ጸሐፊዎች ለኢየሱስ አድርገውታል።

ሐዋርያት

ኢየሱስ በትንሣኤውና በዕርገቱ መካከል ለ40 ቀናት በታያቸው ጊዜ "ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን እንዳስረዳቸው" እርግጠኞች መሆን እንችላለን (ሉቃ. 24፡27)። ይህም ሐዋርያት ክርስቶስን ከቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት እንደሚሰብኩ የተማሩበት ጊዜ ነው። ምናልባት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በዚያን ጊዜ እንዳስተማራቸው ማወቃችን ጥሩ እንደሆነ እናስብ ይሆናል። መደነቅ ያለብን አይመስለኝ። ሐዋርያቶች በሐዋርያት ሥራ ስብከታቸው ያስተምሩናል።

የአዲስ ኪዳን ስብከት ክርስቶስን እንዴት መስበክ እንዳለብን ይመራናል። ከዚህ የምናገኘው ነገር ቢኖር የሐዋርያት ስብከት ሁለት ገጽታ እንዳለው ነው። (1). ክርስቶስን ሰብከዋል። (2). የሰበኩትም ከመጽሐፍ

ቅዱስ ነው። በርግጥ እነርሱ የነበራቸው ብሉይ ኪዳን መሆኑ ግልጽ ነው። የስብከታቸው ይዘት ክርስቶስ ነበር፣ የስብከታቸውም ምንጭ ቅዱሳት መጻሕፍት ነበሩ። ሆኖም እኛ አዲስ ኪዳንም ጭምር አለን፣ ይህም ሐዋርያት ከነበራቸው የበለጠና የበለጸገ ማጣቀሻ መጽሐፍ አለን ማለት ነው።

ለምሳሌ፣ ጴጥሮስን በጰንጠቆስጤ ቀን የተናገረውን እንመልከት፣ ሐዋ. 2፡14-36። በመጀመሪያ በኢየሩሳሌም የነበረውን ክስተት ለማብራራት ኢዩኤልን ይጠቅሳል (ቁ. 14-21) ከዚያም ቀጥሎ ከቁጥር 22-36 ክርስቶስ ለምን እንደሞተና እንደተነሳ በመናገር፣ ከዚህም ጋር በተጨማሪ ኩብሉይ ኪዳን በመጥቀስ - መዝሙር 16 (ሐዋ. 2፡25-28) ዳዊት የተነበየው የጌታ የኢየሱስን ትንሣኤ እንደሆነ አመልክቷል፤ እንዲሁም በመዝሙር 110(2፡34፤35) በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ዳዊት ሳይሆን ክርስቶስ መሆኑን አሳይቷል። ቀጥሎም በሐዋ. 3፡21-25 ጴጥሮስ እንደገና የብሉይ ኪዳን ነብያትን በመጥቀስ ክርስቶስን የክርስቶስን ቀን ያመለክታል።

በሐዋ. 4፡24-31 ላይ አማኞች በጸሎታቸው መዝሙር ምዕራፍ ሁለትን በመጥቀስ የክርስቶስ መሰቀል ከሄሮድስ፣ ከጲላጦስና ከሌሎች ሰዎች ጥምር ተግባር ጋር እንደተዛመደ እናያለን። ይህ በርግጥ ስብከት አይደለም ነገር ግን የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ምን ያህል ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥልቀት እንደሚረዱና እንዴት ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ክርስቶስ የሚጠቁሙ መሆናቸውን እንደሚገነዘቡ ያሳያል። ጳውሎስ በጲስድያ-አንጾኪያ በሚገኘው ምኵራብ ውስጥ ክርስቶስ የቅዱሳት መጻሕፍትን ተስፋዎችና ትንቢቶችን እንዴት እንደፈጸመ አሳይቷል (ሐዋ. 23፡13-41)።

ለአሕዛብ መስበክ

በተጨማሪም ለአሕዛብ በተናገሩ ጊዜ ክርስቶስን አመልክተዋል - ለምሳሌ በአቴንስ - ሐዋ. 17፡24-31። በዚህ ቦታ ጳውሎስ ከቅዱሳት መጻሕፍት አለመጥቀሱን ያስተውሉ፣ ምክንያቱም ለአቴናውያን ብዙም ትርጉም ስለማይሰጥ ሲሆን፣ ነገር ግን ጳውሎስ የሰበከው እግዚአብሔር፣ እንዲሁም የፍርድ እውን መሆን፣ የክርስቶስ ከሞት መነሳት እውነታ እነዚህ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች ናቸው። ሐዋርያት በተሰሎንቄ እና በቤርያ የሰበኩት ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው (ሐዋ. 17፡2፤ 11)፤ በኤፌሶንም እንዲሁ በምኩራብና በጢራኖስ አዳራሽ ከቅዱሳት መጻሕፍት ሰብከዋል፣ “በእስያ አውራጃ ይኖሩ የነበሩት የአይሁድና የግሪክ ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ለመስማት ቻሉ፣ እነዚህም አይሁድና የግሪክ ሰዎች ነበሩ” (19፡8-10)። ከዚያም ወንጌል ወደ ዓለም ሁሉ እንደሚደርስ እርግጠኛ ሆነዋል። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያሳዩት ክርስቶስ የዓለም ሁሉ አዳኝ ነበረ እንጂ

የአይሁድ ብቻ አልነበረም። ስለዚህ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ስለክርስቶስ የተማረው ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው - ሐዋ. 8፡26-35፤ ቆርኔሌዎስ ንስሐን አግኝቷል (11፡18)። የኢየሩሳሌም ጉባኤ የአሕዛብን መዳን በአሞጽ ተመልክቷል (አሞጽ 9፡11፤ 12)፣ (ሐዋ. 15፡16፤17)። በጲስድያ በአንጾኪያ እና በሮም የነበሩ አይሁዶች ወንጌልን በተቃወሙ ጊዜ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት እግዚአብሔር ወንጌልን ለአሕዛብ እንደሚልክ ተነግሯቸዋል(13፡46-48፤ 28፡25-28)።

የሐዋርያት መልዕክት

ከዚህ በተጨማሪ የተለየ መልዕክት ነበራቸው። አይሁዶች ሊያውቁት የሚገባቸው ወሳኝ እውነት ኢየሱስ በቅዱሳት መጻሕፍት ተስፋ የተነገረለት ክርስቶስ መሆኑን ነው። ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ ስብከቱ ላይ እነርሱ የሰቀሉት፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ከሞት ያስነሳው ኢየሱስ በእርግጥም "ጌታና ክርስቶስ" (ሐዋ. 2፡36) መሆኑን የማሳየት ሃላፊነት ነበረበት። ሐዋርያት ይሰብኩበት የነበረው አቋም እንዲህ ነበረ፣ "በየዕለቱም፣ በቤተ መቅደስም ሆነ

በየቤቱ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ከማስተማርና ከመስበክ ከቶ ወደ ኋላ አላሉም ነበር" (ሐዋ. 5፡42) - ይህንንም የሚያረጋግጡት በቅዱሳት መጻሕፍት ነበር። እርሱ ክርስቶስ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅም ነበር - ዮሐ. 20፡31፤ ሐዋ. 9፡20 - ደግሞም ጌታ ነው - 2ቆሮ. 4፡5። ክርስቶስ ማንም ቢሆን፣ እግዚአብሔርን በመግለጥ ያደረገው ነገር ሁሉና ኃጢአተኞችን ማንጻቱ ሁሉ የሚሰበከው ከቅዱሳት መጻሕፍት ነው።

መልእክታት

የቤተክርስቲያን መርህ ክርስቶስን ከጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መስበክ እንደሆነ የወንጌል መጽሐፍትና የሐዋርያት ሥራ ምስክርነቶች ውስጥ ተመልክተናል፤ ደግሞም ሐዋርያትም መልእክታቸውን በሚጽፉበት ጊዜ የክርስቶስን ማዕከልነት በአዲስ ኪዳን ጽሑፋቸው እንዲሁ እናያለን። ለምሳሌ ጳውሎስ የሮሜን መልእክት የሚጀምረው የተለየለትን ወንጌል ለይቶ በማሳየት ነው፤

> “ጳውሎስ፣ የክርስቶስ ኢየሱስ ባሪያ፣ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራና ለእግዚአብሔር ወንጌል የተለየ፤ ስለዚህ ወንጌል በነቢያቱ በኩል በቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞተስፋ ተሰጠ። ወንጌሉም ስለ ልጁ፣ በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ ሆነ፣ በቅድስና መንፈስ ደግሞ ከሙታን በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ስለ ተገለጠው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው” (ሮሜ 1፡1-4)።

በዚህ ቦታ ይህንን እንመለከታለን፤ (ሀ) ወንጌል በብሉይ ኪዳን አስቀድሞ ተስፋ የተነገረለት መሆኑን፤ (ለ) ወንጌል ስለ ክርስቶስ እንደሆነ (ሐ) ክርስቶስ መለኮት (የእግዚአብሔር ልጅ) እና ሰው (ከዳዊት ዘር የመጣ) መሆኑን፣ ይህም ማለት ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ(ብሉይ ኪዳንንም ጨምሮ) የምንሰብከው ኢየሱስ ዘላለማዊ ቃል ብቻ ያልሆነ፣ የሥላሤ ሁለተኛ አካል የሆነና ሰው ሆኖ የመጣ (ተስግዎ) ክርስቶስ መሆን አለበት። ምንም እንኳ ዘላለማዊ ቃል ቢሆንም፣ ዘላለማዊ ቃል ብቻ ግን አልነበረም፣ እርሱም በቅዱሳት መጻሕፍት የተተነበየለት ሥጋ የሆነው ቃል ነው። (መ) ምንም እንኳ በአካል የተገለጠ የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም፣ እርሱ “እንደ ቅድስና መንፈስ ደግሞ ከሙታን በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ተገልጧል”። ትንሣኤው የሚያረጋግጥልን ነገሮች (1) አሁን ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ምኗ እንደሆነና (2) በመከራውና በሞቱ ውስጥ የተፈጸመውን ሥራ ዋጋ ምን እንደሆነ ነው። እርሱ የተሰቀለውና ከፍ ያለ ጌታ ነው፣ ጌታና ክርስቶስም ነው። ሆኖም እርሱ ሁልጊዜ የዘላለም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። በአንደኛ ቆሮንቶስ ውስጥ፣ ክርስቶስ የእኛ የፋሲካ በግ ነው (5፡7)፣ ይህንንም የሚፈጽም ነው (በሚቀጥለው ገጽ ተብራርቷል)፣ እርሱ በምድረበዳ ከሕዝቡ ጋር የነበረው ዓለት ነው (10፡4)፣ ይህም ሰው ሆኖ ከመምጣቱ ከአስራ አራት ምዕት ዓመታት በፊት ነው ( በተጨማሪም ይሁዳ 5 ይመልከቱ)።

በገላትያ 3፡16 ክርስቶስ ለአብርሃም ቃል የተገባለት “ዘር” መሆኑንና ይህም ተስፋ የተፈጸመለት መሆኑን ጳውሎስ አሳይቷል፣ ስለዚህም በሥጋ የአብርሃም ዘር የሆኑት ብቻ ሳይሆኑ አማኞች ሁሉ የአብርሃም ዘሮች ናቸው።

የዕብራውያን መልእክት አስረግጦ ሲነግረን እንዲህ ይላል፣ “እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት በኩል ለአባቶቻችን ተናግሮ፣ በዚህ መጨረሻ ዘመን ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ተናገረን . . . “ (ዕብ. 1፡1፤2)።

ይህ ቃል እግዚአብሔር ጥንት ከተናገረባቸው መንገዶች የተለየ አይደለም፣ ነገር ግን የእነዚያ ትንቢቶች ፍጻሜ ነው። ይህ የእብራውያን መልእክት ክርስቶስ ሰውና አምላክ(መለኮት) መሆኑን፣ የክህነትና የመሥዋዕቶች ፍጻሜ እንደሆነ፣ ክርስቶስ ራሱ ሊቀ ካህናችን መሆኑን፣ የተሻለ ኪዳንን የገኘንበት እንደሆነ ያሳየናል። መልእክቱ በሙሉ የተመሠረተው ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን የሁሉም አይነት ተስፋዎች ፍጻሜ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው (ዕብ. 9፡23፤ 24)።

ጴጥሮስም በበኩሉ ይህንን ሲያረጋግጥ፣ "ለእናንተ ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ ድነት ተግተው በጥንቃቄ ይመረምሩ ነበር፤ በእነርሱ ውስጥ የነበረው የክርስቶስ መንፈስ ስለ ክርስቶስ መከራ እንዲሁም ከመከራው በኋላ ስለሚሆነው ክብር አስቀድሞ በመናገር ያመለከታቸው ጊዜ መቼና እንዴት እንደሚፈጸም ይመረምሩ ነበር" (1ጴጥ. 1፡10፤11) ይላል። በተጨማሪም ጴጥሮስ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" የሚለውን የአብን ድምፅ የክርስቶስ መልክ የተለወጠበት ተራራ ላይ መስማቱን ያረጋግጣል፣ እንዲሁም የትንቢቱን ቃል ቅዱሳት መጻሕፍት "የበለጠ እንዳረጋገጡት" ይገልጻል (2ጴጥ. 1፡16-21)።

ራዕይ በብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ውስጥ ተብራርቷል፣ ይኸውም ከፍ ያለው ክርስቶስን ከብሉይ ኪዳን በተወሰደ አነጋገር "የሰው ልጅ" (ራዕ. 1፡13) በማለት በቤተ መቅደሱ ቅዱስ ስፍራ ያለው፣ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል በመግለጽ ነው። ክርስቶስ ዙፋንን እና መለኮታዊ ክብርን ከአብ ጋር የሚካፈል የእግዚአብሔር በግ ነው (5፡6-14፤

7፡17)። ሐዋርያቱ ቅዱሳት መጻሕፍት ክርስቶስን እንደሚጠቁሙ እና የእነርሱም ሥራ ክርስቶስን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መስበክ እንደሆነ ተረድተው ነበር።

ክርስቶስን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ማየት የእግዚአብሔርን መንፈስ ይጠይቃል

ክርስቶስን ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ማየት ወዲያውኑ የሆነ ነገር አልነበረም። ቅዱሳት መጻሕፍቶቻቸውን በሚገባ የሚያውቁ ብዙ አይሁዶች ይህን አያምኑም። እግዚአብሔር ክርስቶስን ሊያሳያቸውና ሊገልጥላቸው ይገባል። ሐዋርያቱ ክርስቶስን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያዩት አይሁዊ ስለነበሩ ሳይሆን እግዚአብሔር ክርስቶስን ስለገለጠላቸው። ኢየሱስ ከአብ እንደመጣ የጴጥሮስን መልስ ልብ ይበሉ፣ ማቴ. 16፡16፤17።

ኢየሱስ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርሱ የሚመሰክሩ እንደሆኑ ነግሯቸዋል፣ ሆኖም አይሁዶች ወደ እርሱ በመምጣት ሕይወትን ለማግኘት አልፈቀዱም (ዮሐ. 5፡39፤40)።

የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀትን አግኝቶ ነገር ግን ክርስቶስን አለማየት ወይም አለማወቅ እንደሚቻል አይሁዶች በሚያሳዝን ሁኔታ ይመሰክራሉ። ጳውሎስ በሮም የነበሩ ለማመን ፈቃደኛ ያልሆኑ የአይሁድ መሪዎችን ገሥጿቸዋል፤ ሐዋ. 28፡23-28። እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት እንድታምኑና ክርስቶስንም በዚያ ውስጥ እንድታገኙት ሊረዳችሁ ያስፈልጋል። ኒቆዲሞስን አስቡ፣ ደቀ መዝሙር የሆነው (ዮሐ. 19፡39)፣ ነገር ግን በመጀመሪያ በነብዩ በሕዝቅኤል የተነገረውን “አዲስ ልደት” የሚለውን ሐሳብ አልተረዳም (ዮሐ. 3፡11-12፤ ሕዝ. 36፡24-26)። በመንፈስ ቅዱስ የሆነ አዲስ ልደት ክርስቶስን እንድናየውና ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንድንገባ የሚያስችለን መሆኑ እውነት ነው፤ ምክንያቱም አዲስ ልደት በክርስቶስ እናምን ዘንድ ያስችለናል። ቅዱሳት መጻሕፍት ለዘለዓለም ሕይወት ጠቢባን ሊያደርጉን ይችላሉ፣ ሆኖም ይህ የሚሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን ብቻ ነው (2ጢሞ. 3፡15)። ሐዋርያት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ክርስቶስን ለማየት በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተዋል። እኛም እንዲሁ ሳንጸልይና በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ ሳንደገፍ መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም ወይንም መስበክ መጀመር የለብንም።

የሐዋርያዊ ስብከት ማዕከሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው

ስለዚህ እኛም ክርስቶስን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንሰብካለን። አዲስ ኪዳን ኢየሱስን የበለጠ ግልጽ አድርጎ ስለሚነግረን ምናልባትም እኛ የበለጠ እርሱን እንሰብካለን። ነገር ግን ኢየሱስ በመጀመሪያ የተሰበከባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሲሆኑ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ ናቸው።

በብሉይ ኪዳን ያለው ክርስቶስ፣ በአዲስ ኪዳን ያለው ያው ራሱ ክርስቶስ ነው፣ እርሱም ሥጋ-የነሳው (ሰው የሆነው) የእግዚአብሔር ልጅ ነው። በብሉይ ኪዳን እርሱ ገና ያልመጣው ሰው የሆነ ክርስቶስ ነው፣ ሰው ሆኖ አልመጣም፣ ነገር ግን አንድ ቀን የሚመጣ ነው። እንደ ጥላ ሆኖ ነው የምናየው እንጂ አካሉን አናየውም፣ ሚስጥራዊ እንደሆነ ሰው እንጂ፣ ግልጽ ሆኖ አልተገለጠም። ሰው የሆነውን ክርስቶስን መስበክ መቻል ሲሆን፣ ነገር ግን በጥላ መልክ ብቻ ስለተጻፈ፣ ክርስቶስን ከብሉይ ኪዳን መስበክ ልንማር ይገባናል። ክርስቶስን ከአዲስ ኪዳን የምንሰብክ ከሆነ ደግሞ፣ ስጋ-ነስቶ (ሰው ሆኖ) የመጣ እንደሆነ ልንሰብክ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ደግሞ በሕይወታችን በሙሉ ክርስቶስን በእውነት ልንሰብክ ይገባናል።

©ብራና ጎስፐል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***

“ክርስቶስን መስበክ” ማለት ምንድን ነው?

በቀላሉ፣ የእግዚአብሔርን ምክር በሙሉ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በማጣቀስ መስበክ ሲሆን፣ ክርስቶስ ደግሞ የዚህ ማዕከሉ ነው። ሐዋርያት ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑን አስተምረዋል፣ እንዲሁም ሰብከዋል (ሐዋ. 5፡42)።

የእግዚአብሔር ልጅ ወንጌል፣ ይህም ከዳዊት ዘር እንደሆነ ፣ ስለዚህም ክርስቶስ ሰውና አምላክ መሆኑን፣ አሁን የከበረና ከሙታን የተነሳ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ጳውሎ ጽፏል (ሮሜ. 1፡1-4)። የቆሮንቶስ አማኞችን ጳውሎስ እንዲህ ብሎ አጥብቆ ነግሯቸዋል “የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን” (1ቆሮ. 1፡23)፤ እንዲህ ማለቱ ግን ጌትነቱን እንዳይሰብክ አያግደውም (2ቆሮ. 4፡5)። ክርስቶስን መስበክ ማለት ወንጌልን መስበክ ማለት ነው፤ መስቀሉንና ትንሣኤውን መስበክ ነው፤ ትህትናውን መስበክ ነው (ከመፀነሱ እስከ ሞቱ ድረስ)፤ ከፍ ከፍ ማለቱን (ከመስቀል እስከ አብ ቀኝ ድረስ) መክበሩን መስበክ ነው፤ የክርስቶስን ማንነት መስበክ ነው፤ ሥራውንና አስተምህሮውን መስበክ ነው፤ ነብይ መሆኑን መስበክ ነው፤ ካህንና ንጉሥ መሆኑን መስበክ ነው፤ መንግሥቱንና ምጽአቱን መስበክ ነው። ይሄ ሁሉ መሰበክ ያለበት ከሁለቱም የቅዱሳት መጻሕፍት ኪዳናት ውስጥ ሲሆን፣ ለጽሑፉ ትኩረት በመስጠት፣ በጥንቃቄ በመተንተንና በማብራራት ሊሆን ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ ስብከት ማለት ክርስቶስን በጽሑፉ ውስጥ መኖሩን ማሳየት ብቻ አይደለም። ክርስቶስ ሊታወጅ እንዲሁም ለወንዶችና ለሴቶች ለድነታቸው ሊነገር ይገባል።

ስለዚህ ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን መስበክ ማለት ክርስቶስን ከብሉይ ኪዳኑ (ያህዌ/ጌታ) ጋር አንድ መሆኑን አንድ ከማድረግም የሚያልፍ ነው፤ ወይም የጌታ መልአክ ከማድረግም ይበልጣል፤ ወይም የተስፋ ቃል ፍጻሜ መሆኑን

ከማሳየት ይበልጣል፤ ወይም አምሳል መሆኑን በብሉይ ኪዳን ከማረጋገጥ የሚበልጥ ነው። ይህ መደረግ ያለበት ነገር ቢሆንም፣ ከዚህ በተጨማሪም ክርስቶስን ለይቶ የማሳየቱን ጠቀሜታ ለሰዎች ማስረዳት ያስፈልጋል። ክርስቶስን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናሳየው ምሑራዊ ጉብዝናችንን ለመጠቆም ሳይሆን፣ ነገር ግን ለሰዎች መዳን ይሆንላቸው ዘንድ ነው።

ቻርልስ ሃድን ስፐርጀን ዘሶውል ዊነር (*Soul Winner*) በተባለው መጽሐፉ ሲናገር እንዲህ ይላል፣

ክርስቶስን የተሞሉ ስብከቶች ሁሉ በርግጥም አድማጮችን በመለወጥ የሚባርኩ እንደሆኑ አምናለሁ። ስብከቶቻችሁ በክርስቶስ የተሞሉ ይሁኑ፤ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በወንጌል የተሸፈኑ ይሁኑ። ወንድሞቼ ሆይ፣ እኔ በበኩሌ ከክርስቶስና ከመስቀሉ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር ልሰብክ አልችልም፤ ምክንያቱም ሌላ ምንም ነገር ስለማላውቅ ነው፤ ከረጅም ጊዜ በፊት ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው፣ በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም የተሰቀለውን፣ እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና። ብዙ ጊዜ ሰዎች "የስኬትህ ምስጢር ምንድን ነው?" ብለው ይጠይቁኛል። ሁል ጊዜ የምሰጣቸው መልስ ከዚሁ ሌላ የተለየ ምስጢር እንደሌለኝ ነው፤ ወንጌልን ሰብኬአለሁ - እንጂ ስለ ወንጌል አልሰበክሁም። ነገር ግን ወንጌል ሙሉ የሆነ፤ ነጻ፤ ሕያው የሆነው የክርስቶስ ክቡር ወንጌል ሲሆን፤

እርሱም ሰው ሆኖ በመምጣት የተገለጠ የምሥራች ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ስበኩት፤ ወንድሞች ሆይ ሁልጊዜም በሁሉም ቦታና በሁሉም ጊዜ ስትሰብኩ፣ በትምህርታችሁ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በብዛት መኖሩን እርግጠኞች ሁኑ። የአንድን ወጣት ስብከት ስለሰማው የሽማግሌ አገልጋይ ታሪክ ታስታውሳላችሁ፤ ወጣቱ ሰባኪ ሽማግሌው ምን እንደተሰማው ሲጠይቅ፣ ሽማግሌው መልስ ለመስጠት ዘግይቶ ነበር፤ ሆኖም በመጨረሻ እንዲህ አሉት፣ "ምላሽ ልሰጥህ የሚገባ ከሆነ፣ ስብከትህን ሙሉ ለሙሉ አልወደድኩትም፣ በስብከት ውስጥ ክርስቶስ አልነበረም" በማለት መለሱ። ወጣቱም እንዲህ ብሎ መለሰ፣ "ትክክል አይደለም"፣ "ምክንያቱም ክርስቶስ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ መኖሩን አላየሁም አለ"። ሽማግሌው አገልጋይም "እንዴታ፣ በኢንግላንድ ውስጥ ከእያንዳንዱ ትንሽ ከተማ እና መንደር እንዲሁም አነስተኛ ሰፈር ሁሉ ሳይቀር ወደ ለንደን የሚወስድ መንገድ መኖሩን አታውቅምን?" በማለት ጠየቁት። ስለዚህ አንድን ጽሑፍ ባገኘሁ ጊዜ ለራሴ እንዲህ እላለሁ፣ "ከዚህ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወስድ መንገድ አለ፤ እርሱን እስካገኘው ድረስ ጉዞዬን እቀጥላለሁ ማለቱ ነው"። ከዚያም ወጣቱም እንዲህ አለ "ጥሩ ነው፣ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ ምንም የማይናገር ጥቅስ እየሰበክ ቢሆንስ?" ሽማግሌው ሰባኪም፣ "ቀጥዬ በአጥርም ሆነ በቦይ በኩል ሄጄም ቢሆን እርሱን አገኘዋለሁ" አለ።

ወንድሞች ሆይ፣ እኛም እንዲሁ ልናደርግ ይገባል፤ በንግግራችን ሁሉ ውስጥ ክርስቶስ ሊኖር ይገባል፣ በምንናገረው ውስጥ ምንም ነገር ቢኖርም ባይኖርም ማለት ነው። ነፍስ ትድን ዘንድ በእያንዳንዱ

ስብከት ውስጥ ወንጌል በበቂ ሁኔታ ሊነገር ይገባል። ስለዚህ በግርማዊት ንግሥት ፊት እንድትሰብኩ ብትጠሩ፣ እንዲሁም ደግሞ ለቀን ሠራተኞች ወይም ለሊቀመንበሮች መስበክ ቢኖርባችሁ፣ በእያንዳንዱ ስብከታችሁ ውስጥ እውነተኛው ወንጌል መኖሩን ልትጠነቀቁ ይገባል።

**2.** ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን

አንድ ሰባኪ በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ (በሕግ፣ በነቢያት፣ በመዝሙራት፣ በጥበብ መጽሐፍት ውስጥ ማለትም [በኢዮብ፣ በምሳሌና በማሕልየ መሓልይ፣ በመክብብ ውስጥ]፣ በትረካ መጽሐፍት [ለምሳሌ የታሪክ መጻሕፍት] ደግሞም በግጥም መጻሕፍት ውስጥ ክርስቶስን የመፈለግና የማግኘት ልማድ ሊኖረው ይገባል። በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ስለ ኢየሱስ የተጻፉትን ነገሮች ለሰዎች ልንተረጉም ያስፈልጋል። ይህን እንዴት ልንማር እንችላለን? ሲንክለር ፈርጉሰን እንዳሉት፣ ምናልባትም እጅግ የላቁ የመጽሐፍ ቅዱስና የክርስቶስ ሰባኪዎች ሳያስቡ(በደመ ነፍስ) የሚሰብኩ ናቸው . . . የሚጠቀሙባቸውን መርሆች ያዳበሯቸው ሳያውቁ ሲሆን፣ በተፈጥሮ

ችሎታ፣ በሥጦታ፣ ደግሞም በማዳመጥና በመስበክ ልምምዳቸው ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን፣ ክርስቶስን እና ሰዎችን የሚወድ፣ እንዲሁም ወንጌልን ለመስበክ በመፈለግ ለጥሪው ቁራጥ የሆነና(1ጢሞ. 4፡15)፣ ቅዱሳት መጽሐፍትን የሚወድ ልብ በምንም ነገር ሊተካ አይችልም (2ጢሞ. 3፡14) ። እነዚህን ነገሮች ብንረዳም ነገር ግን ደግሞ ሌሎች ብዙ የምንማራቸውና ሊረዱን የሚችሉ ነገሮች አሉ።

ክርስቶስ፦ብርሃናት ሁሉ የሚገናኙበት ማንጸባረቂያ

ሲንክሌር ፈርጉሰን እንዲህ ይላል፦

> በአዲስ ኪዳን መገለጥ ውስጥ እንደቆሙ እና ብሉይ ኪዳንን ወደኋላ እንደሚያዩ ክርስትያኖች፤ ክርስቶስ እንደ ሥነ-ፍታቴያዊ ማንጸበራቂያ ሆኖ ቀርቧል። በእርሱ በኩል ወደኋላ ስንመለከት እንደ ነጭ ብርሃን የሆነውየኢየሱስ ክርስቶስ እውነት አንድነት በብሉይ ኪዳን ውስጥ በህብረ ቀለማት ተከፋፍሎ ይታያል (ዕብራውያን 1፡1 እና 2 ተመልከቱ) ።
>
> ወደፊት ደግሞ ስንመለከት፤ እነዚህ እንደ ብዝሃ ቀለማት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተከፋፍለው የምናገኛቸው የመገለጥ ጥቅሎች በአንድነት እርሱ ላይ ይጋጠማሉ።
>
> ይህንም እውነታ በቅጡ ስንረዳ ፤ እነዚህ የቀለማት ጥቅሎች እንዴት በክርስቶስ ወደ አንድነት እንደሚመጡ እና እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከእርሱ ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ማየት እንጀምራለን።

በዚህ መንገድ እንዴት ብሉይ ኪዳን ወደፊት ወደ ክርስቶስ እንደሚጠቁም እንገነዘባለን።(አንዳንድ መጋቢዎች፤ ገጽ 673)

ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ክርስቶስ ልክ በሁብረ ቀለማት ውስጥ እንደምናገኛቸው ሰባቱ ቀለማት ነው፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ቀለማት በአዲስ ኪዳን በአንድነት በነጭ ብርሃን እንደሚታይ ሙሉ በሙሉ እንደተገለጠ እውነት ናቸው።ራሱ ክርስቶስ ሆኖ አሁን ግን ሙሉ በሙሉ ተገልጧል። አዲስ ኪዳን ላይ ያለው መገለጥ ከብሉይ ኪዳን ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ለማስረዳት ቢ.ቢ ዋርፊልድ የተባለው ሰው የተጠቀመውን ተጨማሪ ምሳሌ እንመልከት። በቤት ዕቃዎች የተሞላ ጨለምለም ስላለ አንድ ክፍል ይናገራል። በጨለማ ውስጥ የነገሮች ቅርጽ እና ጥላ እንጂ የሚታይ ነገር የለም። ልክ የክፍሉን መብራት ስታበሩ ግን ሁሉንም በትክክል ማየት ትችላላችሁ። ስለሆነም ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን የሚታየው ልክ እንደ ቅርጽ እና ጥላ ነው፤ በግልጽ አይታይም። በአዲስ ኪዳን ግን ሁሉም ማየት ይችሉ ዘንድ ግልጽ ሆኗል። ይህን መጨመር ግን ይኖርብናል። አዲስ ኪዳን የቤት ዕቃውን ብቻ ሳይሆን ዝርዝር ባሕርዩንም ጭምር ይነግረናል፤ክርስቶስ ባይመጣ ኖሮ ወንጌል የሚባል ነገር አይኖርም፤ የትኛወም ነገር በራሱ የሚኖረው እውነታ እና ምንነት በጥላ ውስጥ ተሸፍኖ ይኖር ነበር። ታዲያ በተሰግዎ በተገለጠው በክርስቶስ ላይ የሚጋጠሙትን የእውነት ቀለማት የቱ ጋር ነው ማየት የምንጀምረው?

የተስፋ ፍጻሜ

የክርስቶስ መምጣት የጀመረው የቱ ጋር ነው? ወንጌሉስ የሚጀምረው የቱ ጋር ነው? በእርግጥ ጅማሬው ከዘለዓለም ነው፤ ነገር ግን እስኪ እግዚአብሔር መገለጥን በሰጠበት በጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ እስቡት፤ ለዚህ ደግሞ ወደ ዘፍጥረት 3፡15 መሄድ ይኖርባችኋል። ከውድቀት በኋላ፣ እግዚአብሔር ለእባቡ በተናገረው ነገር ውስጥ “በአንተና በሴቲቱ፣ በዘርህና በዘሯ መካከል፣ ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ።” ሲል ተስፋን ሰጠ። ይህ ራሱን እጅግ ዋጋ በሚያስከፍለው መንገድ ሰይጣንን ስለሚቀጠቅጥ አዳኝ የተሰጠ ተሰፋ ነው። በሰይጣን ዘር እና በሴቲቱ ዘር መሃል በታሪክ ውስጥ የተገለጥ ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሞት እና ትንሣዔበግልጽ የሚታይ እና ፍጻሜን ያገኘ በተጨማሪም በዳግም ምጽዓቱ ድምዳሜን የሚያገኝ ጠላትነት አለ።

ዘፍጥረት 3፡15 በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሌሎች ተስፋዎች ሁሉ የተገኙበት "የተስፋዎች እናት" ነው ልንለው እንችላለን። ከዚህ ጊዜ አንስቶ ፤ ከሔዋን ወንድ ልጆች በመጀመር ታሪክ ራሱ እባቡን የሚገድለውን "ወንድ ልጅ" ፍለጋ ላይ ነው። ጌታ አምላክ የእስራኤልን ሕዝብ እንደ "በኩር ልጅ" አድርጎ በጉዲፈቻነት በመውሰድ ከግብጽ ባርነት ነጻ አውጥቶታል (ዘጸ 4፡22 ፣ 23 ፤ ሆሴ 11፡1)። በጊዜ ሂደት ውስጥ መሲሕ ተብሎ ተጠርቷል (2ሳሙ 7፡16 ዘለዓለማዊ ንጉስ ፣ የተቀባ)፤ ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ይህ ተስፋ እየተገለጠ ሲመጣ ማንነቱ ዘርፈ ብዙ ሆኖ ወይም በብዙ ቀለማት ያሸበረቀ ሆኖ እናየዋለን።እስኪ በዚህ መልኩ ተስፋ የተሰጠውን ወንድ ልጅ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ፈልጉት ፤ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ በእርግጥ ክርስቶስን ለማግኘት ትቃረባላችሁ።

ስለሆነም የክርስቶስ መምጣት በተሰጠው ተስፋ አውድ ውስጥ መታየት እንዳለበት እንመለከታለን።ከእግዚአብሔር ዕቅድ ሂዳት ጋር ፈጽሞ በማይሄድ መልኩ፤ የሆነ ጊዜ እንደ ንጉስ፤ አንዴ ደግሞ እንደ ካህን፤ ወይም እንደ መልዓክ "ብቅ" ስለሚልሰው ሳይሆን የምንሰብከው፤ ወደ እኛ በተለያየ መንገድ ስለመጣ፣ ነገር ግን ይህን ሲያደርግ ሁልጊዜ የወደፊቱን የመምጣቱን ተስፋ ይበልጥ ሙሉ እንዲሆን እና እንዲፈጸም ስላደረገ ሰው ነው። ስለዚህ ክርስቶስ በዋናነት በቅዱሳት መጻሕፍት ስለራሱ የተሰጡ ተስፋዎችን የፈጸመ ነው ብለን ልንናገር እንችላለን።ሲንክሌር ፈርጉሰን ክርስቶስሲመጣ እግዚአብሔር የወሰነለትን ሥራ በመፈጸም ተስፋውን "በመሙላት ሙሉ አድርጎታል" ብሏል። በመጀመሪያ ሲመጣ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ከጫፍ አድርሶታል፤ ነገር ግን በዳግም ምጽዓቱ አጠቃላይ የታሪክ እና የእግዚአብሔር ዕቅድ ይፈጸማሉ።

ኪዳን

ተስፋ አንድ ነገር በእርግጥ እንደሚሆን ማረጋገጫ ነው። ተስፋ ሰጪው ተስፋውን ለመፈጸም ሃይሉም ሆነ ፈላጎቱ ካለው ደግሞ፤ ተስፋው እጅግ አስተማማኝ ይሆናል ማለት ነው። በእግዚአብሔርም የሆነው እንዲሁ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር እምነት የሚጣልባቸውን ተስፋዎች ከመስጠትም በላይ ያደርጋል። የእንቁ ፈርጦች በወርቅ ሳህን ላይ እንደሚቀመጡ ሁሉ እንዲሁ እነዚህንም ተስፋዎች በኪዳኑ ውስጥ አስቀምጧል።

©ብራና ጎስፔል ፎከስ ሚኒስትሪ *2022*

በትዳር ውስጥ ቃል ኪዳን የሚገቡት አካላት አንዳቸው ለሌላቸው ቃል ብቻ ሳይሆን የሚገቡት፤ በቅድምያ አንዳቸው ለሌላቸው ራሳቸውን ለመስጠት ነው ኪዳን የሚገቡት።እግዚአብሔርም እንዲህ ነው የሚያደርገው።የኪዳኑም አንኳር ሃሳብ “አምላክ እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ” የሚለው ራሱ ተስፋ የሆነው ንግግር ነው (ዘሌ 26፡11 ፤ ኤር 31፡33 ፤ 32፡38 ፤ ራዕይ 21፡4)። ክርስቶስ መታየት ያለበት በኪዳን አውድ ውስጥ ነው። አዳም ከእግዚአብሔር ጋር በተለምዶ “የሥራ ኪዳን” በተባለ ኪዳናዊ ግንኙነት ውስጥ ነበር። ይሄ በአዳም ፍጹም እና ዘለቄታዊ መታዘዝ ላይ የተመሰረተ እግዚአብሔር ያልተሳተፈበት ከዚህም የተነሳ በጸጋ የተሞላ ኪዳን ነበር (ዘፍ 2፡16 ፣ 17)። እግዚአብሔርን በፍጹምነት ቢታዘዝ ኖሮ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ህብረት የጸና ይሆን ነበር። ነገር ግን አልታዘዝም። ስለሆነም እባቡን ይገድለዋል ተብሎ በሚጠበቀውአዳኝ ተስፋ ውስጥ እንዳየነው እግዚአብሐየር የጸጋን ኪዳን መሠረተ።የኪዳኑ ማዕከላዊ ሃሳብ እርሱ የሕዝቡ አምላክ መሆኑ እና እነርሱም ደግሞ የእርሱ ሕዝብ መሆናቸው ነው። ይሄ በሥርዓት ተመስርቶ የምናየው በበረከቱ ተስፋዎች (ዘፍ 12፡1-3 ፤ 13፡14-17 ፤ 15፡13-16 ፤ 17፡1-14 ፤ 22፡19)እና ከአብርሃም የሚጠበቀው የመታዘዝ መስፈርቶች ላይ ነው (17፡1 ፤ 9 - 14)። በመቀጠልምበሙሴ በኩል በሲና ምድረበዳ በኪዳኑ ውስጥ ላለው ሕግ የአምልኮ እና የመታዘዝ ምላሽ እንዲኖር ድንጋጌዎች ተሰጡ (ዘጸ 19፡4-6 ፤ 20፡1-17፤ 24፡1-11) እንዲሁም ከዳዊት ጋር ስለ መሲሐዊው ንጉስ ተስፋ ተሰጠ (2ሳሙ 7፡12-16)። በመጨረሻም፤ በኤርምያስ የተነገረው አዲሱ ኪዳን (31፡31-34) በኢየሱስ ፤ እርሱም ባፈሰሰው ደም ተከናወነ (ማቴ 26፡26-29 ፤ ዕብ 8፡1-13) በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ ተስፋ የተነገረለት መሲሑ ራሱ በእግዚአብሔር ለሕዝቡ የተሰጠ ኪዳን እንደሆነ ተነግሯል (49፡8)። በእርሱ በኩል፤ እግዚአብሔር እና ሕዝቡ ጸጋ በተሞላበት ህብረት ለዘለዓለም አንድ ሆነዋል።የሙሴ ኪዳን የተሰጠው በመሀከለኛ ነበር ይሄም መሀከለኛ ደግሞ ሙሴ ነበር፤ አዲሱ ኪዳን ግን መሀከለኛ የለውም፡ እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር መለኮት ነው፣ እኛ ደግሞ በክርስቶስ በኩል ዘላለማዊ አምላክ ከሆነው ከሥላሴ ጋር ወደ አንድነት መጥተናል (ገላ 3፡19 ፣ 20)። የኪዳኑ ማዕከል እግዚአብሔርን ለሰዎች የሚገለጠው እና ሰውን እና እግዚአብሔርን የሚያስተሳሰረው እርሱ መሆኑ ነው።

ስለዚህ ኪዳኑን ሳይሰብኩክርስቶስን መስበክ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው። እርሱ፤ አዳም የወደቀበትን የሥራ ኪዳን ፍጹም በሆነ መታዘዝ የፈጸመ እንዲሁም የኪዳኑ ቅጣት የሆነውን ሞት በመስቀሉ የተሸከመ ነው (ዘፍጥረት 2፡16 ፣ 17)። የእግዚአብሔርን ሕግ ፈጽሞ ታዞአል፤ ፈጹም በሆነ ጽድቁም ምክንያት የጸጋን

©ብራና ጎስፐል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***

ኪዳን አምጥቶአል። ጽድቅን ሁሉ ፈጽሟል (ማቴ 3፡15) ይህንን በማድረግም የሰማይ አባቱን ታዞአል (ዩሐ 17፡3)። የአዳም ተምሳሌታዊ ፍጻሜ ነው (ሮሜ 5፡14)፣ የመጨረሻው አዳም፤ ሁለተኛው ሰው (1ቆሮ 15፡45 ፣ 47)፣ በእርሱ እኛ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ እርሱ ለእኛ ኃጢያት ሆነ። የአዳም ኃጢያት ሰውን ሁሉ ወደ ሞት መራ፤ የክርስቶስ መታዘዝ ደግሞ የሚያምኑትን ሁሉ ወደ ሕይወት ይመራል (ሮሜ 5፡18-21 ፤ 1ኛ ቆሮ 15፡22)። በእርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ዘላለማዊ ኪዳን ውስጥ ነን።

ወደ አዲሱ ኪዳን በሚጠቁም መልኩ በብሉይ ኪዳን ያለው ክርስቶስ

ክርስቶስ አዲሱን ኪዳን ላይ ያለውን መገለጥ በሚጠቁም መልኩ በብሉይ ኪዳን በአራት መንገዶች ተገልጧል ማለት እንችላለን። በቅድምያ

ትንቢት

ይሄንን አስቀድመን በሐዋርያው ስብከት ውስጥ ተመልክተናል። "በእግዚአብሔር የተሰጡ ተስፋዎች ሁሉ፣ "አዎን" የሚሆኑት በእርሱ ነውና" (2ቆሮ 1፡20) "እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት በኩል ለአባቶቻችን ተናግሮ፣ በዚህ መጨረሻ ዘመን ግን ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ተናገረን "(ዕብ 1፡1 ፣ 2) ትንቢት በእርግጥ በአንድ ጎኑ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን እንደሌለ እና ገና የሚመጣ እንደሆነ ያሳየናል። ይሁን እንጂ ትንቢት ገና "በሙላት እስኪሞላ" ድረስ ብዙ ፍጻሜ ያገኙ ተስፋዎችን ግን መዘንጋት የለብንም። ለምሳሌ፤ አብርሃም ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆን የተሰጠው ተስፋ (ዘፍ 12፡1-3) እስራኤል በግብጽ እያለ በከፊልም ቢሆን ተፈጽሟል። ሙሉ በሙሉ የተፈጸመው ግን በቤተክርስትያን እና በአዲሱ ፍጥረት ነው። ነቢያቶች የዘዳግም 18፡15 ፤ የነገስት ፤ የ2ኛ ሳሙኤል 7፡12-15 ከፊል ፍጻሜዎች ናቸው።

ሁለተኛ

አምሳላዊ(Typology)

ጳውሎስ በሮሜ 5፡14 ላይ አዳም "ይመጣ ዘንድ ላለው አምሳሉ (ቱፖስ) ነበር" ይለናል (ክርስቶስ ማለት ነው) ቱፖስ የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ አምሳል ወይም ንድፍ የሚለውን ሃሳብ ይሸከማል፤ ይሄም ብቻ ሳይሆን ግን ከከባድ ምት በኋላ የቀረ ምልክት፤ በማሕተም የተቀረጸ ወይም ደግሞ በቀለም ውስጥ በኃይል ተነክሮ የቀረ በብረት የተሰራ ቅርጽ ሊሆን ይችላል። አሁን በምናወራው ሃሳብ፤ አዳም አምሳሉ ሲሆን ክርስቶስ ደግሞ (ምስሉ የሚያርፍበት) ጠንካራው ነገር ነው (ክርስቶስ "እውነተኛው አዳም" ነው፤ ምንም እንኳን አዳም በታሪክ ውስጥ

የእውነት የነበረ ሰው ቢሆንም)። አዳም በታሪክ ውስጥ የነበረ ሰው ነው፤ በእርሱ ስለ ክርስቶስ የምንማረው ነገር አለ። በአዳም እና በክርስቶስ መሃል ትይዩነት ወይም መመሳሰል (Analogy) አለ። ይህን በተመለከተ ሁለቱም ለሁለት የሰው ዘርራስ ናቸው፤ አንዱ የኃጢያት እና ሞት ጀማሪ ሲሆን፣በእርሱም የሆኑት በኃጢያት እና በሞት እስራት ውስጥ ናቸው፤ ሁለተኛው ደግሞ የሕይወት እና የጽድቅ ምንጭ ሆኖ በእርሱ የሆኑት ይህንን የሚያጣጥሙ ናቸው። ሁለት ራሶች አሉ፤ የሰው ዘር ወይ አዳም ውስጥ ወይ ደግሞ በክርስቶስ ውስጥ የሚመደብ ነው፤ በዚህ ረገድ መመሳሰሉ አዎንታዊ ነው፤ አዳም የሰራው ጠፍቶ ክርስቶስ በሰራው መተካቱ ማለትም አለመታዘዝ በመታዘዝ፣ ኃጢያት በጽድቅ፣ ሞት በሕይወት መተካቱ ነገሩ አሉታዊ ጎን እንዳለው አመላካች ነው። አዳም ምሳሌ ሲሆን ክርስቶስ ደግሞ የምሳሌው ፍጻሜ እንደሆነ ተነግሯል፣ ይኸውም የምሳሌው ጥላ የተመሰረተበት እውነታ ማለት ነው።

የአምሳል ሃሳብ፡- 1. እግዚአብሔር የሚሰራው በሚደጋግማቸው ተመሳሳይ አካሄዶች ነው- መጀመሪያ አዳም በመቀጠል ክርስቶስ 2. በአምሳልና በአምሳሉ ተፈጻሚ በሚያደርገው መሃል እድገት አለ (አንዳንዶች ይሄን “እመርታ” (escalation) ይሉታል፤ ግሬዳኑስ ስብከት፣ ገጽ 249) ። ምሳሌውን የሚፈጽመው ወይም ምሉዕ የሚያደርገው ምሳሌ ሆኖ ከቀረበው እጅግ የበለጠ ነው። ብሉይ ኪዳንን የምናነበው እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ እየሰራ እንዳለ እና የተሻለው ነገር ደግሞ ወደፊት እንደሚመጣ በማሰብ ነው።

እንደ አምሳል የሚታዩት ነገሮችን በተመለከተ ገዢ የሆነው መርኽ ምንድነው? መርኹ ሁሉም ነገር በክረስቶስ ላይ ፍጻሜውን አያገኝም የሚል ነው፤ ነገር ግንበአጠቃላይ የድኅነትን ሥራ እና የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲሁም የክርስቶስ አካል እና ሙሽሪት ያጠቃልላል።

እንደ አምሳል የምናያቸው ነገሮች ምናልባት፡-

- ሰው ይሆናሉ፡- ኖኅን መመልከት እንችላለን፤ ኖኅ ለመዳን እግዚአብሔር የተጠቀመበት መሣሪያ ነው፤ ይሄም ብቻ ሳይሆን እንደገና በጥፋት ውሃ በፀዳው ፍጥረተ ዓለም ላይ “አዲሱ አዳም” ነው፤ ይሄ ደግሞ ሊመጣ ላለው ለክርስቶስ ምሳሌ ይሆናል ፣ አብርሃም የጸጋ ኪዳን ራስ ነው ፣ ያዕቆብ ራሱ እየቆሰለ ከእግዚአብሔር ጋር በመታገል እና በማሸነፍ ክርስቶስን ያሳየናል ፣ ዮሴፍ ያለአግባብ በሰዎች መበደሉ እና መከራን በመቀበሉ የሕዝቡ ፤ የሕዝቡም ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብ ሀገራት ሁሉ አዳኝ

ለመሆን ከፍ ከፍ ብሏል ፣ ሙሴ በዘጸዓት ሕዝቡን ከእስራት ያላቀቀ እና እግዚአብሔርን ወደማምለክ ነጻነት እና ወደተስፋይቱ ምድር የመራ ሰው ነበር፤ እንዲሁም ወደ እውነተኛው ነቢይ የሚጠቁም ነቢይ እና ሕግ ሰጪ

ነበር (ዘዳ 18፡15 ፤ ሐዋ 3፡22)፤ ኢያሱ ጠላቶቹን ያሸነፈ እና ሕዝቡን ወደ ተስፋይቱ ምድር ያስገባ ሰው ነበር፤ ዳዊት ንጉሰ የነበረ እና በሰው ቋንቋ ለመናገር የኢየሱስ የዘር ግንድ እንዲሁም የኢየሱስ ንግስና ምሳሌ የነበረ ነው። ሌሎች ብዙ ክርስቶስን የምታዩባቸው አነስ ያሉ ምሳሌዎች አሉ፤ ለምሳሌ እንደ መልከጼዲቅ ፣ መሣፍንቶች ፣ ቦዔዝ ፣ አስቴር ፣ ነህምያ።

- ተቋማት፡ እንደ መቅደሱ አይነት (የመቅደሱ ጥላነት በክርስቶስ ምልዐትን አግኝቷል - ማቴ 12፡6 ፤ ዩሐ 2፡19) ፣ እንዲሁም በራሳቸው ተስፋ የሰጡትን ነገር መፈጸም የተሳናቸው (ዕብ 10፡1-9) ነገር ግን ወደፊት ሊሆን ያለውን የክርስቶስን ሞት የሚጠቁሙት መስዕዋቶች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ ክርስቶስ እንደ ፍጻሜ የሆነለት የክህነት አገልግሎት፤ ይኸውም አሉታዊ በሆነው ንጸጽር ከአሮን እና ከሌዋውያኑ ካህናት ጋር ሲሆን አዎንታዊ በሆነው ንጸጽር ደግሞ ከመልከጼዲቅ ጋር የሚታይ ነው (ዕብ 4፡14 – 5፡10 ፤ 7፡11-28)

- ክስተቶች ፡ ኖህ እና ቤተሰቡ በመርከቡ ውስጥ ሆነው ያገኙት መዳን (ዘፍጥረት 7፡8) ፤ ወይም የዘጸዐት ታሪክ ለምሳሌ በሉቃስ 9፡31 ላይ ኢየሱስሊያደርገው ስላለው በኢየሩሳሌም “ስለ መውጣቱ” ይናገራል። የድኅነት ሥራን በተመለከተ ምሳሌውን በብሉይኪዳን ነቢዩ ኢሳይያስ ተጠቅሞ እናያለን (43፡2 ፤ 11፡15፣ 16 ፤ 48፡21 ፤ ኤርምያስ 23፡7 ፤ 1ቆሮ 10፡1-5) ወይም የአብርሃም ተወዳጅ ልጅይስሐቅመስዕዋት ሊሆንበት የነበረው ክስተት (ዘፍ 22፡11-19)።

- ምልክቶች፡ (ወደ ሆነ ነገር የሚጠቁሙ ምልክቶች)ለምሳሌ የእሳት እና የደመናውን አምድ ብንወስድ በአንድ ጎኑ የእግዚአብሔር መታየት (Theophany) የተገለጠበት ደመና ነው(ዘጸ 23፡20) በሌላ ጎኑ ደግሞ በሕዝቡ መሀከል የተገኘው የጌታ ክብር አምሳል ሲሆን በክርስቶስ በተለይም ደግሞ መልኩ በተለወጠበት ተራራ (ማቴ 17፡5) እና በዕርገቱ (ሐዋ 1፡9-11) ተፈጽሟል እንዲሁም በዳግም ምጽዓቱ ሙሉ በሙሉ ይፈጸማል (ዳን 7፡13 ፤ ማቴ 24፡30) ። ሌላ ደግሞ፡ ወደሞት አፋፍ የደረሱት

እስራኤላውያን በማየት ይፈወሱበት የነበረውን የነሃሱን እባብ ማየት እንችላለን (ዘኁ 21፡9 ፤ ዩሐ 3፡14)

- በታዎች ፡ የእግዚአብሔር ቤት የተባለው ቤተል (ዘፍ 28፡10-22 እና ዩሐ 1፡51)

ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ቀን "ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል እንዲህ ተብሎ የተነገረ ነው…" ብሏል (ሐዋ 2፡16) "ይሄ… እንዲህ የተባለው ነው" የሚለው አነጋገር በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ክርስቶስን ለመተርጎም

ቁልፍ መንገድ ነው። አንድ ምሁር "በቅዱሳት መጻሕፍት የምናየው አምሳል እና ስለወደፊት የተነገረ ትንቢት በመሠረተ ሃሳብ አንድ ሲሆኑ፤የሚለያዩት በቅርጽ ብቻ ነው" ብሏል። (ሙርሂድ በአይኤስቢኢ መጣጥፍ ላይ ስለ "አምሳል" (Type)) ከጻፈውና መርኾች/ *Principles* በተሰኘው መጽሐፍ ገጽ 145 ላይ ቤርክሆፍ እንደጠቀሰው) ይሄ ማለት "አምሳል" (Type) የሚታይ ወይም የሚጨበጥ ትንቢት ነው። በቃል፣ በተግባር ወይም በምልክት ስለክርስቶስ ማለትምሥራውን በተመለከተ ስለ ጥልቀቱ እና ስፋቱ፤ ወይም ስለ ቤተክርስትያን በአጠቃላይ የተነገረው ትንቢት የተፈጸመው በመጀመሪያው መምጣቱ ነው "በእግዚአብሔር የተሰጡ ተስፋዎች ሁሉ፣ "አዎን" የሚሆኑት በእርሱ ነውና…" (2ቆሮ 1፡20) ጥላው የሚገኘው በብሉይ ኪዳን ሲሆን፤ አካሉ ደግሞ በአዲሱ ኪዳን ነው (ዕብ 8፡5 ፤ 10፡1)።

ሦስተኛ

የእግዚአብሔር መታየት *(Theophany)*

አምሳላዊ (Typology) የምንለው ሃሳብ፤የእግዚአብሔር መታየት (Theophany) ወይም እግዚአብሔር አምላክ ሰው ከመሆኑ በፊት በአካላዊ መገለጥ (ዘፍ 3፡8 ፣ 17፡1-22 ፤ ዘፀ 34፡5-9) ምናልባትም የሥላሴ ሁለተኛው አካል ሰው ከመሆኑ በፊት (ዘፍ 16፡7-13 ፤ ዘጸ 23፡20 ፤ ዘፍ 32፡22-32 ፤ ሆሴ 12፡3-4 ፤ መሳ 6፡11-24 ፣ 13፡3 ፣ 21-23) እንደ እግዚአብሔር መልዓክ ከታየበት ሃሳብ ጋር መለየትአለበት።"ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም፤ ነገር ግን በአብ እቅፍ ያለው አንድያ ልጁ የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው።" (ዩሐ 1፡18) የሚለው ቃል በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የሚሰራ መርህ ስለሆነ፤ ከላይ ያየናቸው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መታየቶች/መገለጦች ናቸው ማለት ነው።በተወሰነ መልኩም ቢሆን ) በብሉይ ኪዳን ላይ ያለው የእግዚአብሔር መታየት (Theophany) የእግዚአብሔር አካላዊ መገለጥ ፍጻሜ የሚያገኝበት እና ጸንቶ የሚቀርበት የአምላክ-ሰው መሆን (Incarnation)አምሳል (Type) ነው።

©ብራና ጎስፐል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***

ታሪክ

ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ወደ አዲሱ ኪዳን የሚጠቁምበት አራተኛው ማስረጃ ታሪክ ነው። እግዚአብሔርበታሪክ ውስጥ የገለጣቸው፤ በክርስቶስ መምጣት እና በወንጌሉ ፍጻሜን ያገኙ እውነቶችን የያዙተደጋጋሚአካሄዶች አሉ። ሙሴ በፈርዖን (ዘጸ 2፡1-10) እንዲሁም በእግዚአብሔር (ዘጸ 4፡24-26) ሊገደል ከጫፍ መድረሱ በሰው ቋንቋ ስናወራ የእግዚአብሔርን ድካም የተሞላው አካሄድ እና የመሲሑን ተሰባሪነት ያሳዩናል። ወይም ደግሞ ሳምሶን በገዛ ሕዝቡ ለፍልስጤማውያን ታልፎ መሰጠቱ ከዛም መታሰሩ በኋላም ደግሞ ታላቅ ድል ማግኘቱን ማየት እንችላለን (መሳ 15፡11-15) ድካም በሚመስል መንገድ የተገለጠው ብርታት፤

በሽንፈት መንጋጋ ውስጥ የተገኘው ድል፤ እንዲህ አይነቶቹ ተመሳሳይ አካሄዶች በክርስቶስም በተደጋጋሚ የታዩ እና ፍጻሜን ያገኙ ናቸው። ሁሉም ባይሆኑ እንኳን ብዙ ጊዜ አምሳል ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ። እዚህ ጋር በማቴዎስ (1፡1-17) እና በሉቃስ (3፡23-38) ላይ የምናገኛቸው የዘር ሃረግ ዝርዝሮችንም ጨምረን ማየት እንችላለን።

ማቴዎስ “ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ” የሚለውን ሃረግ “አምሳል” (Type) ብለን እንደ ምንጠራቸው እንደ መቅደሱ የመስዕዋት ሥርዓቶች ወይም ኢሳይያስ 53 ላይ የሚገኘውን ሃሳብአይነት ከማሳየት ባለፈ በብሉይ ኪዳን ላይ ያሉ ክስተቶችን ጠቃሚ በሆነ መልኩ በኢየሱስ ሕይወት ላይ ለማዋል ይጠቀምባቸዋል። ለምሳሌ፡ በማቴዎስ 2፡15 ሆሴዕ 11፡1 በመጥቀስ “ልጄን ከግብጽ ምድር ጠራሁት” ይላል። ማቴዎስ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ተደጋጋሚ አካሄድ እንዳለ ያሳየናል። የእግዚአብሔር “ልጅ” የሆነው እስራኤል (ዘፀ 4፡22) በዘጸዓት ከግብጽ እንደወጣ እናያለን በተመሳሳይ መልኩ የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጅ እና እውነተኛው እስራኤል ወደ ግብጽ ከወረደ በኋላ ከጥፋት በመዳን ከግብጽ እንዲወጣ ይደረጋል። እዚህ ጋር በክርስቶስ እና በሕዝቡ መሃል ያለውን ተመሳሳይነት እንመለከታለን። ሲንክሌር ፈርጉሰን እንዲህ ይላል “ይህን በማድረግ፤ ማቴዎስ አጠቃላይ የዘጸዓትን ትርክት የምናነብበትን እና የምናብራራበትን ማዕከለ-ክርስቶሳዊ (Christocentric) ቁልፍ ይሰጠናል (አንዳንድ መጋቢያን፣ 678) ሞትን እና ትንሣዔንስ በተመለከተ የኢየሱስ ወደ ግብጽ መውረድ እና ከግብጽ መውጣቱ ውስጥ የተወሰነ ፍንጭ አይተያንም? በተመሳሳይ መልክ፤ ማቴዎስ ትንቢተ ኤርምያስ 31፡15 ላይ የሚገኘውን በቅ.ክ.ል 587 ምርኮ ተደርገው ወደ ባቢሎን

©ብራና ጎስፐል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***

ለተወሰዱት እስራኤላውያን የተነገረውን ቃል በመውሰድ በሔሮድስ ለተገደሉት ሕጻናት ይጠቀመዋል "የልቅሶና የታላቅ ዋይታ ድምጽ፣ በራማ ተሰማ፤ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፤ መጽናናትም አልቻለችም፤ ልጆቿ ሁሉ አልቀዋልና።" (ማቴ 2፡18)። ራሔል በምርኮ ጊዜ ለልጆቿ እንደምታለቅስ የእስራኤል እናት ሆና ተስላለች። የኤርምያስ 31 አውድ ከተመለከትን ግን የመጽናናት ሃሳብ የያዘ ነው፤ የሚቀጥለው ቁጥር እንዲህ ይላል "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ድምፅሽን ከልቅሶ፣ ዐይኖችሽንም ከእንባ ከልክ…" ማቴዎስ እንዴት ከቅዱሳት መጻሕፍት የእስራኤል ብሔራዊ ማንነት የጀመረበትን የዘፀዓት ታሪክ እና የምርኮ ወይም የእስራኤልን መጨረሻ የምናይበትን ታሪክ ማጣቀሻ አድርጎ እንደሚጠቀም አስተውሉ።

በእነዚህ ሁለት ክስተቶች ሲንክሌር ፈርጉሰን እንዳመለካተን ቅዱሳት መጻሕፍትን "አምሳላዊ" (Typical) ከሆነ አጠቃቀም በተለየ እንዴት ማዕከለ-ክርስቶሳዊ (Christological) በሆነ መንገድ መጠቀም እንደምንችል እናያለን። ሌላው ምሳሌ ያዕቆብ በመጀመሪያው የኢየሩሳሌም ጉባዔ ላይ አሞጽ 9፡11፣12 ወንጌልን በተመለከተ እንዲህ ብሎ ይጠቅምበታል "የፈረሰውን የዳዊትን ቤት እገነባለሁ። ፍርስራሹን መልሼ አቆማለሁ፤ …ይኸውም የቀሩት ሰዎች ጌታን እንዲፈልጉ፣ ስሜን የተሸከሙ አሕዛብም እንዲሹኝ ነው…ጌታ እንዲህ ይላል" (ሐዋ 15፡16፣

17) በመጨረሻም ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን በብዙ መንገድ ጥላ ሆኖ ቀርቧል፤ በአዲስ ኪዳን ግን አካሉ ነው። አንዳንዶች እንደሚሉትከብሉይ ኪዳን ጋር ያለውን ግንኙነት ማድረግ የምንችለው አዲስ ኪዳን ላይ በቀጥታ ጸሐፊዎቹ ከተጠቀሙት ብቻ ነው በሚል ያለልክ ገደብ ማስቀመጥ የለብንም። ነገር ግን ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ እና በጥንቃቄ በትክክል ግንኙነቱን ለማድረግ መሞከር አለብን።

ልጁን በተመለከተ የሚደረግ ፍለጋ

ከላይ ባነሳሁት ሃሳብ ላይወደፊት ስለሚመጣው እባቡን ስለሚገድለው ልጅ የተሰጠው ተስፋ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ማዕከላዊ የሤራ ሃሳብ ነው ብያለሁ። ይሄ ደግሞ እየፈለግን ያለውን ማየት እንድንችል ይረዳናል። ልጁ በተለያየ መገለጫዎች እና መልኮች ነው የቀረበው ፤ ይህ የሆነው ግን እንዲሁ ለጨዋታ ሳይሆን ማንነቱ እጅግ የሚያስደንቅ፤ ሁለገብ እና በአንድ ቅርጽ ብቻ ሊሳል እስከማይችል ድረስ የበለጸገ በመሆኑ ነው። ከላይ እንደገለጽናቸው ስሞች አይነት፤ ኢየሱስ ደሙ ለፍርዳችን ሳይሆን ነጻ ለመውጣታችን የሚጮኸውን መከራ ተቀባዩ አምላኪ እንዲሁም የተሻለው እና እውነተኛው አቤል ሆኖ እናየዋለን (ዕብ

12፡24)፤ ወይም ደግሞ ኢየሱስ ምንም አይነት እንስሳ በቦታው እስከማያስፈልግ ድረስ ለእኛ ሲል የታረደውን እውነተኛ ይስሐቅ ነው (1ኛ ቆሮ 10፡1-4) ኢያሪኮ ከመውደቋ በፊት ኢያሱን የተገናኘው ለሕዝቡ ጠባቂ የሆነው፤ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ነው (ኢያሱ 5፡13-15)፤ በኢሳይያስ ላይ ያሉት "የሎሌ ዘማሪዎች" ላይ ያለው ሎሌ በተለይም ደግሞ በኢሳይያስ 53 ላይ ያለውን ስቅዩ ሎሌ ነው፤ የሰላም አለቃ የሆነው እውነተኛው ሰለሞን (ማቴ 12፡42) እንዲሁም በማሕልየ መሓልይ ላይ ያለችው ውዴ ተብላ የተጠቀሰችው ሱላማጢስን ማየት እንችላለን። ብሉይ ኪዳን ድል የሚያደርገውን እና የሚያሸንፈውን "ልጅ" ፍለጋ ላይ ነው። በተዓምራት ስለተወለዱት እና መካን ስለነበሩት ሴቶች ብዛት እስኪ አስቡ፤ ለሳራ ፣ ለርብቃ ፣ ለራሔል እና የሳምሶን እናት እንዲሁም ሐና የተሰጡአቸውን ልጆች አስቡ። ኢየሱስ እንዲህ አይነት "ልጅ" ነበር። የብሉይ ኪዳን ቀለማት በእርሱ ብርሃን ላይ ይጋጠማሉ፤ በብሉይ ኪዳን ላይ ያሉት "ምስሎች" ሕያው የሆነውን እውነታ ጠቋሚ ነበሩ።በብሉይ ያሉት የተለያዩ ምስሎች ወደ አንድ ፍጹም አካል ይመጣሉ፤ ይሄም አካል የእግዚአብሔር ልጅ መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

አዲሱ ኪዳን እያለ ከብሉይ ኪዳን መስበክ ለምንድነው ያስፈለገው? በብሉይ ኪዳን ሥራውን እና ማንነቱን በተመለከተ ነጠላ ገጽታዎችን ማየት ስለምንችል ነው። ለምሳሌ፡- ዘጸዓት እና ከዛ በኋላ የተከናወኑ ክስተቶች ግልጽ በሆነ እና ሁለገብ በሆነ መልኩ፤ በክርስትና ያለውን የድኅነት ሃሳብ እና የኃጢያትን ውጤት ያሳዩናል። ክርስቶስ የሠራው የመስዕዋትነትን ሥራ በአዲሱ ኪዳን ከምታገኙት በላይ በዘሌዋውያን መጽሐፍ ላይ በተሟላ መልኩ ሊታያችሁ ይችላል። የነቢይነት፣ ክህነት እና ንግስናን ሃሳቦች ከአዲስ ኪዳን ይልቅ በብሉይ ወለል ብለው

ይታያሉ። መከራውን እና ምትካዊ የስርየት ቅጣቱን በተመለከተ ከአዲስ ኪዳን ከየትኛውም ክፍለምንባባት ይልቅ በኢሳይያስ 53 ላይ ብዙ ሃሳብ ማየት ትችላላችሁ። ከአዲስ ኪዳን ይልቅ በመላዓለሙ ላይ እንደሚገዛ መዝሙር 72 ላይ ወይም የተወሰነ የነቢያት መጻሕፍት ክፍል ላይ ውብ በሆነ መልኩ ቀርቦ ታገኛላችሁ፤ ይሄም ብቻ ሳይሆን ሊመጣ ስላለው የእግዚአብሔር ቀን አስደናቂ በሆነ አገላለጽ ተነግሮ ታገኛላችሁ (ኢሳ 2፡6 ፤ ሶፎ 1፡14-16)። ስለዚህ ይሄ የሚያሳየን በእርግጥ ከብሉይ ኪዳን መስበክ እንዳለብን ነው። ነገር ግን ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን ላይ በሙሉነት ተገልጧል ደግሞም ተብራርቷል፤ ከዚህ በምናገኘው ብርሃን ነው ብሉይ ኪዳንን የምንሰብከው።

©ብራና ጎስፔል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***

ነገሩን በትክክል ማግኘት

ያየናቸው በርካታ ምሳሌዎች የሚያስተምሩን ነገር ቢኖር፤ ክርስቶስ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን "ውስጥ" እንዳለ ሙሉ በሙሉ ከተቀበልን በኋላ ልንሰብከው እና የጌታችንን እና የሐዋርያቱን ፈለግ በመከተል ከቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ልናውጀው እንደሚገባነው። ይሄ ማለት ግን እያንዳንዱ ስብከት የአንድ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል በማተት መጀመር አለበት ማለት አይደለም፤ ለዚህ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በአቴንስ ያደረገውን ለምሳሌነት ማየት ይቻላል። ነገር ግን የሚሰበከው ክርስቶስ ግን "በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት" የሚገኝ መሆን አለበት።

እዚህ ጋር እየሞከርኩ ያለሁት ሥነ-ስብከትን ለማስተማር አይደለም ፤ ስለዚህ ይህን በተመለከተ መስጠት ያለብኝን ተግባራዊ አስተያየቶችን ከመስጠት ተቆጥቤ ስብከታችን እንዴት ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ መሆን እንደሚችል እናገራለሁ።

አንደኛ፡- መሠረታዊ መርኾችን አስታውሱ፡ ተደጋጋሚ የተስፋ ፍጻሜን አካሄዶችን ማየት፤ ክርስቶስን በተስፋ እና በኪዳን አውድ ውስጥ መስበክ፤ ክርስቶስ ብዝሃ ቀለማቱ በአንድ የሚጋጠሙበት ማንጸባረቂያ መሆኑን ማስተዋል። "እርሱም፣ `ከእናንተ ጋር በነበርሁበት ጊጊ፣ በሙሴ ሕግ፣ በነቢያትና በመዝሙር መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው` አላቸው።" (ሉቃስ 24፡44)

ሁለተኛ፡- ከብሉይ ይሁን ከአዲስ ኪዳንየምትሰብኩበትን ክፍል ምንባብ፤ በአውዱ መሠረት ለመረዳት ሞክሩ። ክፍለ ምንባቡ ዛሬ ላለነው ለእኛ ምን ትርጉም ይሰጠናል ከማለታችሁ በፊት በመጀመሪያ ለተጻፈላቸው ሰዎች ምን አይነት ትርጉም እንዳለው ተረዱ። ጸሐፊው ምን ሊያስተላልፍ ነው የፈለገው?

ሦስተኛ ፡- ወደ ክርስቶስ የሚያመራ "ምሉው ትርጓሜ" አለ (የሥነ-መለኮት ምሁራን የቅዱሳት መጻሕፍት ሴንሰስ ፕሌኒዮር ብለው የሚጠሩት ማለት ነው) ይሄ ትርጓሜ ሰው በሆነው ጸሐፊ የታሰበ ሳይሆን፤ በእግዚአብሔር የታሰበ ነው። ይሄ ግልጽ የሚሆነው ተነጥሎ በሚታይ ክፍለ ምንባብ ውስጥ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል አጠቃላይ እና

ሙሉ መገለጥ ውስጥ ብቻ ነው። ጴጥሮስ ነቢያቱ በጽሑፎቻቸው ውስጥ ስለ ክርስቶስ የሚናገር አንዳች ሃሳብ እንዳለ ገብቷቸው፤ ይበልጥ ለመረዳት ይተጉ እንደነበር ተናግሯል። (1ኛ ጴጥ 1፡10-12) ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል (የትረካ፣ የሕግ፣ የትንቢት ወይም የቅኔ መጽሐፍ ይሁን) በአግባቡ መረዳት የሚቻለው

©ብራና ጎስፐል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***

በቅድሚያ የክፍለምንባቡን ታሪካዊ እና ሰዋሰዋዊ ገጽታውን ግልጽ ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው። "ሙሉ ሃሳቡ" ከታሪካዊ-ሰዋሰዋዊ ገጽታው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ክርስቶስን እና ማንነቱን ከመረዳት አንጻር ግን ሰፋ ያለ ነው። ሉዊስ ቤርክሆፍ እንዲህ ይላል "የቅዱሳት መጻሕፍት ጥልቅ ሃሳብ ስለሚባል ጉዳይ ማውራት ይቻላል ወይ የሚልጥ ጥያቄ ቢነሳ፣ መልሱ አዎ ነው የሚሆነው። ነገር ግን የቅዱሳት መጻሕፍት ጥልቅ ሃሳብ የምንለው ሌላ ሁለተኛ ወይም የተለየ ሃሳብ አለው የሚለውን አይወክልም። በሁሉም ረገድ በቅዱሳት መጻሕፍት ቀጥተኛ እና አግባብ ያለው ሃሳብ ላይ የተመሠረተ ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት ትክክለኛ ትርጉም ሁልጊዜ ላይ ን በማየት ብቻ አይገኝም።(ፕሪንሲፐልስ፣ ገጽ 59፣ አጽንዖት የደራሲው ነው)። "ጥልቅ ሃሳብ" የምንለው የብሉይ ኪዳንአምሳል (Type) ፣ ተምሳሌቶች (Analogy) እና ተደጋጋሚ አካሄዶች (Pattern) በክርስቶስ መንፈሳዊ ግዛት፣ በሥራዎቹ እና በአዲስ ኪዳን ላይ ፍፃሜ ሲያገኙ ማለት ነው። ይህን ግልጽ በሆነ መልኩ የሚያሳየን ጳውሎስ "ዘር" የሚለውን በነጠላ ወይም በብዙ ልንጠቀመው የምንችለውን ቃል ለአብርሃም ከተሰጡት ተስፋዎች በመውሰድ (ዘፍ 13፡15፣16) ነጠላ እንደሆነ አድርጎ እና በክርስቶስ ፍጻሜን እንዴት እንደገኘ የተናገረበትን ስንመለከት ነው። (ገላ 3፡16)ለአብርሃም ከተሰጠው ሌጣ ተስፋ ባለፈ ይሄ ምሉው ሃሳቡ ነው ማለት ነው። ይሄ ማለት ግን የተለየ ትርጓሜ ተሰጥቶት አይደለም፤ ይልቁን የታሪካዊ-ሰዋሰዋዊ (Historical – Grammatical)ገጽታው ሰፋ.ቶ እና ምሉዕ ትርጓሜውን አግኝቶ ነው።

አራተኛው፡ ምንም እንኳን ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ክርስቶስ ቢመሩንም፤ ሁሉም ግን እኩል በሆነ መልኩ እና በቀጥታ ይመሩናል ማለት ግን አይደለም። ቻርለስ ስፐርጅን፣ በእንግሊዝ ሃገር ከአነስተኛ እና ቦታ ከማይሰጠው ከአንድ ገጠር ተነስቶ ወደ ለንደን መምጣት ይቻላል፤ ነገር ግን ከተለያዩ ቦታዎች ስንመጣ በቅድምያ ጠባብ በሆነ መንገድ ከዛም ሰፋ ወዳለ መንገድ መሻገር በመቀጠልም ወደ ዋናው መንገድ መውጣት በመጨረሻም የመኪና መንገዱ ላይ መድረስ (በስፐርጅን ጊዜ ባይኖርም!) ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው ወደ ለንደን ጉዞ የሚጀመረው። ከተለያዩ ሥፍራዎች የመኪናው መንገድ ቀጥታ ይወስዳችኋል። እያንዳንዱ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍለምንባቦች ወደ ክርስቶስ በቀጥታ ይወስዱኛል ብላችሁ አትጠብቁ። ነገር ግን ቀጥታ ያልሆነ መንገዶችን ስታገኙ ጉዞው የተሳሳተ እንደሆነም ማሰብ የለባችሁም። ቅዱሳት መጻሕፍትን በታማኝነት ተጠቀሟቸው፤ ነገር ግን ቤርክሆፍ እንዳለው ፤ ሁልጊዜ ትክክለኛው ትርጉም ጥልቀ ሳይገባ ወለሉ ላይ በቀላሉ አይገኝም።

©ብራና ጎስፐል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***

አምስተኛ ፡ ብሉይ ኪዳንን የምንሰብክበት የተለመደው መንገድ ሥነ-ምግባራዊ እና ተግባራዊ ትምህርቶችን በመስጠት ነው። ይሄ በራሱ የተሳሳተ ላይሆን ይችላል፤ በዚህ መንገድ ግን የቅዱሳት መጻሕፍትን የበለጸገ እና ምሉው ትርጉም ማግኘት አንችልም። ይሄ አይነቱ አካሄድ ወደ ክርስቶስ መድረስ ያቅተዋል። ለምሳሌ፡ - በ1ኛ ሳሙኤል ላይ የምናገኘውን የዳዊት እና ጎልያድ ታሪክ ስንሰብክ፤ የታወቀው የስብከት አይነት ዳዊት ታላላቅ ተግዳሮቶችን እግዚአብሔር ላይ ባለው እምነት ተጋፍጧል፤ እኛም ተግዳሮቶቻችንን በእምነት ልንጋፈጣቸው ይገባል የሚል ነው። ይሄ ስህተት አይደለም፣ ነገር ግን ታሪኩ ይሄን ብቻ ሊያስምረን ነው የተጻፈው ብላችሁ ታስባላችሁ? በዚህ ውስጥ ክርስቶስ የታለ? እኔ በምኖርበት በእንግሊዝ ሀገር በሚገኝ ገጠር ውስጥ በዋናው መንገድ ላይ ለእግረኞች የተዘጋጀ ድልድይ አለ። በድልደዩ ስር በመንገዱ ዳር የእግረኞች መንገድ አለ። ከድልድዩ ቀጥታ ወደታች ወደ እግረኞች መንገድ መሄድ ከፈለኩ ምን ላርግ? አንዱ ያለኝ አማራጭ መዝለል ነው። ቶሎ ያደርሰኛል ነገር ግን ሕመም የተሞላበት እንዲያውም አደገኛም ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ወደ ከድልድዩ ቁልቁል ወደ እግረኞች መንገድ የሚወስደውን መሄጃ ተከትዬ ልወርድ እችላለሁ። ይሄም ማለት ወደ 45 ሜትር ገደማ በመንገዱ ሄጄ ወደ እግረኞች መንገድ ለመድረስ በድልድዩ ስር የተወሰነ እራመዳለሁ። ይሄ አካሄዴ ረዥም ሊሆን ይችላል ነገር ግን በብዙ እጥፍ የሚክስ ነው። ክርስቶስን በመስበክም ተመሳሳይ ነው። ቀጥታ ሳይሆን የተወሰኑ መንገዶችን የሚያስኬደን አካሄድ እጅግ ተመራጭ ነው። በቅድሚያ ከክፍለ ምንባቡ ወደክርስቶስ መንገዱን ተከትለን መሄድ ይኖርብናል ከዛም ተመልሰን በመምጣት ተግባራዊ ሃሳቦችን እንሰራለን። ይሄ አካሄድ ረዥም ቢሆንም በመጨረሻ ላይ ግን በብዙ ይክሰናል። ቅዱሳት መጻሕፍትን ልክ በድልድዩ ዙሪያ እንደተሰሩት በእግር እንደሚወረድባቸው መንገዶች ለትክክለኛው ዓላማ ልንጠቀምባቸው ይገባል።

ስድስተኛ አንድ ምሳሌን አስመልክተን ስናስብ በምሳሌውና በምሳሌው ፍፃሜ መካከል ያለውን ተመሳሳይነት መለየት አለብን። ሉዊስ ቤርክሆፍ እንዳለው (i) በምሳሌውና በምሳሌው ፍፃሜ (ምሳሌው የሚያመለክተው) መካከል የሚታወቅ ትክክለኛ የመመሳሰል ነጥቦች መኖር አለባቸው (ii) ይህ ምሳሌ በእግዚአብሔር የተነደፈው ምሳሌ ስለመሆኑ (መርሆዎች፣ ገጽ 145) የሚገልፁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ሊኖሩ ይገባል (እንደ መደጋገም ወይም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጥቅም ላይ የመዋል)። ለምሳሌ የነሐስ እባብ ምሳሌ ነው ምክንያቱም ልክ የተሰቀለው ክርስቶስ በእምነት እንደሚያድን ሁሉ የነሐሱም እባብ ከፍ ሲልና በእምነት ሲታይ ያድናል፤ እርሱ (ለምሳሌ) ነሐስ ስለሆነ የጥንካሬ ምልክት አይደለም። በምሳሌ መጽሃፍ የሚገኙ ምሳሌዎችን ለመተርጎምም ተመሳሳይ መርሆዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። የንጽጽሩ ዋና ዋና ነጥቦች መገንዘባችንን

ማረጋገጥ ይኖርብናል። ከአንድ በላይ የማነጻጸሪያ ነጥብ ሊኖር ይችላል፤ ለምሳሌ ደጉ ሳምራዊ ሃይማኖትና ሕግ እኛን ማዳን ሲሳናቸው ስለ እኛ ከማሳብ የሚያልፈውና ለድነታችን ዋጋ የከፈለው የክርስቶስ ሥዕል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ነገር ግን ሁለቱ

ሳንቲሞች ሁለቱ ሁለቱ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች አይደሉም። ይህ የሚሆነው ከምንባቡ ቁጥጥር ውጪ ስንሆን ነው። ውሃውን ለማጣፈጥ ወደ ውሃ የተወረወረው ዛፍ (ዘጸ 15፡25) የመስቀሉ ምሳሌ ወይም በረዓብ መስኮት የተንጠለጠለው ቀይ ገመድ የማዳን ደም ምሳሌ የመሆኑ ነገር አጠራጣሪ ነው (ኢያሱ 2:18) ነገር ግን እናንተ "በተመሳሳይ መልኩ መስቀል ከመራራነት ውስጥ ጣፋጭነትን ያወጣል" ወይም ምናልባት ቀይ ቀለም ከቁጣ የሚጠብቀንን ደም ሊያስታውሰን ይችላል ልትል ትችላላችሁ። ይህ ማለት ግን እንጨቱ ወይም ገመዱ ወደ መስቀሉ ለመጠቆም በእግዚአብሔር የታሰበው ነው ወይም በምሳሌዎቹና በክርስቶስ ከኃጢያት የመዋጀት ስራ መካከል ጠንካራ መመሳሰል አለ ማለት አይደለም። የብሉይ ኪዳንን ማንኛውንም ዕቃ ወስዶ "ይህ መስቀል ነው" ወይም "ኢየሱስ ነው" ወይም "ቤተ ክርስቲያን ነች" ማለት እንድምታ ነው እንጂ ታይፖሎጂ(አምሳላዊ) አይደለም።

ሰባተኛ በአምሳሉና በአምሳሉ ፍፃሜ መካከል ያለውን ልዩነት ማስታወስ አለብን። አንደኛው ነገሩን የሚፈጥር እውነታ ሲሆን ሌላው ደግሞ የተፈጠረው ነገር ጥላ ነው። ‹ከአምሳሉ ወደ አምሳሉ ፍፃሜ መሸጋገር ከሥጋዊው ቅድመሃሳብ ወደ ንጹሕ መንፈሳዊ ነገር ከፍ ማለት ነው፤ ከውጫዊው ወደ ውስጣዊው፣ ከአሁኑ ጊዜ ወደ መጪው ጊዜ፣ ከምድራዊው ወደ ሰማያዊው መውጣት ነው።› (ቤርክሆፍ፣ መርሆዎች፣ ገጽ 147/ Berkhof, *Principles*, p 147)። የሚያድነው የአምሳሉ ፍፃሜ ነው እንጂ አምሳሉ አይደለም። ከኃጢአት የሚያነጻው የክርስቶስ ደም ብቻ ነው እንጂ የበግ ወይም የፍየል ደም አይደለም (ዕብ 10፡1-4)። በሲናው አሮጌ ኪዳን መሰረት አማኝ እስራኤላውያን የዳኑት በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል በማመን ነበር ነገር ግን የዳኑት ሰውነቱና ስራው በመሥዋዕቱ በምሳሌ በተገለፀው በሚመጣው አዳኝ ነበር እንጂ በመሥዋዕቱ አልነበረም። በወንጌል የዳኑት በሕግ ሳይሆን በሕጉ ጊዜ የወንጌል የማዳን ኃይል (ካልቪን እንደሚለው፣ *ኮመንታሪዮን ኤርምያስ 31፡31-34/ Commentaryon Jeremiah 31:31-34*) ከወንጌል ወደ ሕግ 'ተላልፏል'። የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በዚህ ድነዋል። ነገር ግን የቃል ኪዳናቸው አስተዳደር በእንስሳት ደም እና በየዕለቱና በየአመቱ ሊደገም በሚችል መስዋዕት ከኃጢአት ሊያድናቸው እንደማይችል ይረዱ ነበር። አምሳሎቹ በጉድለታቸውና በድግግሞሻቸው እውነተኛ ነገር እንዳልሆኑ ራሳቸው አሳይተዋል (ዕብ 10፡1-4)።

©ብራና ጎስፐል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***

ስምንተኛ ክርስቶስንና ወንጌልን በመግለጥ ብቻ አትቁሙ። በንስሐና በእምነት የነፍስ ድኅነት መልእክትን ተግባራዊ አድርጉ። ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ዕለት ሰሚዎቹን እንዴት እንደሞገታቸው ተመልከቱ፤ ኃጢያተኛ መሆናቸውን ተረድተው ሲጮኹ እንዲህ ሲል አዘዛቸው "ንስሓ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ" (ሥራ 2:38)። ነፍሶች በእለቱ በመንግሥቱ ላይ እንደ ተጨመሩ ሁሉ እግዚአብሔር ለእኛም ነፍሶችን ይስጠን።

**3** ክርስቶስን የመስበክ ምሳሌዎች

የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች

በብሉይ ኪዳን እባቡን የሚገድለውን ወልድን መፈለግ ዋና ሃሳብ ሆኖ ቀጥሏል። በአዲስ ኪዳን ወልድ መጣ። የእኛ ድርሻ ደግሞ እርሱን ከሁለቱም ኪዳናት መስበክ ነው። ይህንን ክፍለ ጊዜ አንዳንድ ምሳሌዎችን በማየት እናሳልፋለን።

ዘፍጥረት **11፡1-9 -** የባቢሎን ግንብ

በሰው ኩራት ላይ የተደረገ የእግዚአብሔር ፍርድ

የምዕራፍ 10 እና 11ን ቅደም ተከተል እናስተውል። ዘፍ 10 ለምን እንደተከፋፈሉ ከመናገሩ በፊት የተከፋፈሉትን ሕዝቦች ይገልጻል። ይህም ማለት ፍርዱን ከማየታችን በፊት የእግዚአብሔርን መልካምነትና ከጥፋት ውሃ በኋላ የተደገመውን በረከት እናያለን ማለት ነው (9፡7)።

በዘፍ. 11፡1-9 ውስጥ አምስት ትዕይንቶች አሉ (i) ቁ 1፣2 - አንድነትን ያጎላል። ነገር ግን ሰዎች (የተሻለ ከነበረው 'ወደ') ወደ ምስራቅ ይጓዛሉ። ከእግዚአብሔር ራቁ? (ii) ቁ 3፡4 ጡብ መስራት፣ ከዚያም ከተማና ሰማይ የሚደርስ ግንብ ሠርተው ለራሳቸው ስም ለማቆም አሰቡ። ግን ለማንም ሰው ስም ሊያቆም የሚችል ማን ሊሆን ይችላል? እግዚአብሔር ያቆማል። ይህንን ለራሱ በዘፀአት አድርጓል (ኢሳ 63፡12፣ ነህ 9፡10፣ ኤር 32፡20)። የአብርሃምን ስም (12፡2) እና የዳዊትን ስም(2ሳሙ 7፡9) ከፍ ከፍ አደረጓል። ሴም ማለት ስም ማለት ነው - አብርሃምና ዳዊት ከሴም ዘር ናቸው (11 ቁ 10 ይመልከቱ)። በመጨረሻም ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነው ስም የጌታ ኢየሱስ ስም ነው (ፊሊ 2፡9-11)። ከዚህም በላይ ክርስቶስ ብቻ ሰማይንና ምድርን አንድ ያደርጋል። ከሰማይ ወደ ምድር የወረደው እርሱ ነው ደግሞም ወደ ሰማይ ያረገው እርሱ ብቻ ነው – (ዮሐ

1፡51፤ 3፡13)። (iii) የታሪኩ ዋና ነጥብ፡ ጌታ ይወርዳል የሚል ነው። (iv) እግዚአብሔር እስከ ክርስቶስ ምጽአት ድረስ በሰዎች አመጽ ላይ ልጓም አድርጓል (2ተሰ 2፡6-8)፤ 'እኛ' የሚለው የሚያመለክተው ሥላሴን ነው (ቁ 7)። (v) እግዚአብሔር መበተን ያልፈቀደውን ሕዝብ ይበትናል። ቋንቋቸው የተደበላለቀ ነው። በዕብራይስጥ ባቤል ማለት ግራ መጋባት ማለት ሲሆን ለባቢሎናውያን ደግሞ የአማልክት በር ማለት ነው። ባቢሎን በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ የዓለም ተቃውሞ ምልክት ትሆናለች (ኤር 50፣51፤ ራዕ 17-19)። ነቢያት ግራ መጋባት እንደሚሆንና ግብፃውያን የከነዓንን ቋንቋ የሚናገሩበት ጊዜ እንደሚመጣ ተንብየዋል (ኢሳ 19፡18-25፤ ሶፎ 3፡9-10)። ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ሰዎችን ሁሉ ወደ ራሱ እንደሚስብ ቃል ገብቷል (ዮሐ 12፡20-22፤ 31-32)። ወንጌል ለአሕዛብ ሁሉ ይደርሳል (ሉቃ 24፡47፤ ሥራ 1፡8)። በበዓለ ኀምሳ ዕለት "በዚህ ጊዜ ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ ሁሉ" (ሥራ 2፡5) ወንጌሉን በራሳቸው

ቋንቋ እንዲረዱ የብዙ ቋንቋዎች እንቅፋት ተወግዷል። የሴም፣ የካምና የያፌት ዘሮች ተዘርዝረዋል (2፡9-11)። ሁሉም መንፈስ ቅዱስን ካፈሰሰው ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ የተነሳ ነው (2፡33)።

ያን ሁሉ በአንድ ስብከት ላታስቀምጡት ትችላላችሁ ነገር ግን ይህ ክርስቶስን ያማከለ ስብከት ከብሉይ ኪዳን እንዴት እንደሆነ እንድታዩት እንደረዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ - ማለትም ክርስቶስን መጥራት ወይም እርሱን መጠቀም ብቻ ሳይሆን ወንጌልን መስበክ፣ የእግዚአብሔር ታሪካዊ የማዳን ሥራ ሙላት ይህም ክርስቶስን የትኩረት ማዕል ያደረገ ሃሳብ ነው።

ኦሪት ዘፍጥረት **37**

የዮሴፍ ሕልም እና መከራ

በቤተሰቡ ላይ የወደፊት ገዥ የመሆን ህልም አለው። ይሁዳ የሚያደርገውን እያደረገ ነው "የአባትህ ልጆች በፊትህ ተደፍተው ይሰግዱልሃል" (49፡8)። ይሁዳ የመሲሑ የዘር ግንድ ነው። ዮሴፍ ከባድ ፈተናዎችን አሳልፏል ነገር ግን ሕልሞቹ የተነበዩትን ለማየት በግብፅ ውስጥ ከፍ ከፍ አለ። ክርስቶስም በመስቀሉ ላይ ካለው ውርደት ጋር ተደራራቢ ሆኖ ከፍ ከፍ ማለቱና ክብሩ እስኪጀመር ድረስ ክህደትን ጨምሮ በውርደት ውስጥ (ህይወቱን ሙሉ) አልፏል (ዮሐ 13፡31)። ከፍ ሲልም ለቤተሰቡ ብቻ ሳይሆን ለአለምም አቅራቢ ይሆናል። ዓለም የተባረከው በአብርሃም ዘር ነው (41፡57-42፡3፤ 12፡2፣3)። ይልቁንም በእውነተኛው የአብርሃም ዘር ዓለም ይባረካል (ገላ 3፡16)።

**መሳፍንት 13-16 (በተጨማሪም ዕብ 11፡32 ተመልከት)**

ሳምሶን

ምንም እንኳን ግልጽ ኃጢአቶቹ ቢኖሩበትም በዕብራውያን 11 “የእምነት ቋሚ ምስክሮች” ዝርዝር ውስጥ የገባ ሰው ነው። እርሱ የክርስቶስ ምሳሌ ነው ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር የሚቃረን ብዙ ነገር ይኖራል - ምናልባትም ከወትሮው የበለጠ! እርሱ የክርስቶስ ምሳሌ ካልሆነ ታዲያ ስለ እርሱ የተነገሩት ትረካዎች ፋይዳቸው ምንድን ነው? በእርግጠኝነት እርሱን ስለመምሰል አይደለም። እና እርሱ ልክ እንደ በምስል እንደሚታተሙ መጽሐፍት ጀግኖች ለጥቂት እፎይታ ነው የተፃፈው? አይደለም፣ እርሱ የሕዝቡ ገዥ ነበርና ወደ ክርስቶስ አመልክቶናል። ያድናል ወይም ይልቁንም እግዚአብሔር በብዙ ወይም በጥቂቶች ማዳን እንደሚችል ያሳያል። ጌዴዎን የነበረው 300 እንኳ አያስፈልገውም ነበር፤ እግዚአብሔር, በሳምሶን አማካይነት በአንድ ሰው ይሰራል።

በሳምሶን ሕይወት ላይ የተላለፈውን ፍርድ አስታውሱ “ሳምሶንም በፍልስጥኤማውያን ዘመን በእስራኤል ላይ ለሃያ ዓመት ፈራጅ ሆነ” (15፡20)። ለቀናት ፈራጅ ሆኖ ተዋጊ በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ መሪ ሳይሆን ተዋጊ ሆነ፣ ወታደሩን የሚያንቀሳቅስ ሳይሆን ትልቅ ጦርነትን ብቻውን የሚዋጋ ሰው ነበር። ከኢየሱስ ሕይወት ጋር ተመሳሳይነቶች አሉ፤ ለምሳሌ በጌታ መልአክ የተነገረ ተአምራዊ ልደት (መሳ 13፡3፣ ይስሐቅ – ዘፍ 18፡10 ያነፃፅሩ)፤ ከውልደት ጀምሮ የተለየ - ለሕይወት ናዝራዊ ሆኖ የተለየ (መሳ 13: 4፣5)። የኢየሱስ መወለድ የበለጠ ተአምረኛ ነበር፤ እንዲሁም በመልአኩ የተነገረ ሲሆን (የጌታ መልአክ አይደለም) ከተፀነሰበት ጊዜ ጀምሮ ቅዱስ ነበር (ሉቃ 1፡30-35) ደግሞም በውስጥ ቅድስና ለእግዚአብሔር ተወስኗል (ዮሐ 4፡34፤ 17:4) ይህም በውጫዊ ሥነ ሥርዓት ብቻ አይደለም ይልቁንም በመንፈስ ቅዱስ የታገዘ ነበር (13:25፤ ሉቃ 4:1)፤ እንዲሁም እርሱ በገዛ ወገኖቹ ተከድቷል (15፡12)። ነገር ግን የእግዚአብሔር ኃይል በድካም ፍጹም እንደ ሆነ እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ሕይወትን ከሞት መንጋጋ ውስጥ እንደሚያወጣ በሳምሶን አይተናል። ሳምሶን ታላቅ ጀብዶችን ሰርቷል - አንበሳውን ገነጣጠሎ፣ የሠላሳ ሰዎችን ምርኮ በአስቀሎ ወሰደ፣ የፍልስጥኤማውያንን እርሻ አቃጠለ፣ በኤታም መታቸው፣ 1,000 ሰዎችን በአህያ መንጋጋ ገደለ። እነዚህ በጠላቶች ላይ ታላቅ ሥራ ነበሩ። ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነው ፍልስጥኤማዊቷን ሴት በመሻት ነበር፤ ከአንድ ከፍልስጥኤማዊት ጋለሞታ ጋር አንድ ሌሊት ካሳለፈ በኋላ የጋዛን መቃኖች ይዞ ሄደ። ከደሊላ ጋር ሆን ብሎ

©ብራና ጎስፐል ፎከስ ሚኒስትሪ *2022*

በመጋባቱና በተደጋጋሚ በማመንታቱ ናዝራዊ ሆኖ የተሰጠበትን ነገር አጣ ራሱን በዚህም ጥንካሬውን አጣ። ነገር ግን ይህ ወደ እስር ቤት ወሰደውና በመጨረሻ ላይ ከህይወቱ ይልቅ በሞቱ የገደለው በለጠ (16፡30)። የይሁዳ ሰዎች በያዙት ጊዜ ነበር ከገመዱ ነፃ የወጣውና 1,000 ሰዎችን የገደለው፤ እንዲሁም በዚያው የሞት ቦታ ሌሒ (‘ጃውቦን’) እግዚአብሔር የሕይወትን ውሃ ሰጠው (15፡19)።

ከሞት የተገኘ ሕይወት፣ ድል በሞትና በሞት በኩል፣ ድክመት (የገዛ ወገኖቹ እስረኛ እንደመሆኑ) በጠላት ላይ ወደ ድል ተለወጠ፣ ሳምሶን በሥነ ምግባሩ ወይም ለእግዚአብሔር ባሳየው መታዘዝ የክርስቶስ ምሳሌ አልነበረም። ቅድስናው ውጫዊ ከመሆኑ ውጪ እምብዛም ነበር። ነገር ግን እርሱ የእምነት ሰው ነበር - ዕብራውያን 11፡32 ይህን ይነግረናል ስለዚህ እኛም ማመን አለብን። እግዚአብሔርን አመነ እግዚአብሔርም ኃይል ሰጠው። የሳምሶን አስፈላጊነት በያዘው አገልግሎትና እግዚአብሔር ያንን አገልግሎት ያከበረበት መንገድ ነው እንጂ ሳምሶንን በግሉ አስፈላጊ ሆኖ አይደለም። ይህም ሳምሶንን በስነ ምግባር ድክመቱ ተጠቅሞ ለህዝቡ መዳንን ያስገኘና በጠላቶቹ ላይ ፍርድ ያሰጠ ነው። እስራኤል ተዋጊ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ሳምሶን የእግዚአብሔር ሰው ነበር። እግዚአብሔር ጠላቶቹን ድል ለማድረግ የሳምሶንን ቅድስና ሳይሆን ኃጢያቱን ደጋግሞ ተጠቅሞበታል። እርሱ እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ወሰን የሌለውን ታላቅ መዳን ያስገኘለትን ታላቁን ገዥና አገልጋይ የሚያመለክት ጉድለት ያለበት ገዥና

የሕዝቡ አገልጋይ ነበር። በተጨማሪም እግዚአብሔር ዓላማውን ለማስፈጸም ድካማችንን እንኳ እንደሚጠቀም ያሳየናል። የክርስቶስ ድካም ሥነ ምግባራዊ አልነበረም ነገር ግን ወደ ሞት ተወስዷል በመስቀል ላይ ተቸንክሯል፤ ከሁሉም በጣም ደካማ በሆነበት በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር ታላቅ ስራውን አከናወነ። የብሉይ ኪዳን ሊቅ ኤድመንድ ክላውኒ የሳምሶን ታሪክ “…እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በታጠቀ በአንድ ሰው በኩል በሕዝቡ ጠላቶች ላይ እንዴት ፍርድ እንደሚያመጣ ለማሳየት ነው። የሳምሶን ድክመትና ኃጢአት የሚያገለግሉት በእራሱ ህይወትና በእስራኤል ፈራጅነት መካከል ያለውን ልዩነት ከፍ ለማድረግ ብቻ ነው። የተጠራነው የሳምሶንን በጎ ምግባር እንድናደንቅ ሳይሆን እምነቱን እንድናውቅ ነው። ኃይሉ የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ ያውቅ ነበር እናም እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ እንዲፈርድ እየለመነ በእምነት ሞተ (ዕብ 11፡13፣32-34)” (የተገለጠው ምስጢር፣ አይቪፒ፣ 1988፣ ገፅ 141/ *The Unfolding Mystery*, IVP 1988, p141)። የሚሳካው የእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ነውና በዘመኑ ሳምሶን የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር። አንድ ቀን ፍጹሙ አገልጋይ ይመጣል።

©ብራና ጎስፔል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***

**1ኛ ሳሙኤል 17**

ዳዊት እና ጎልያድ

ቁልፍ ምንባብ፡ 'ሰውን ምረጡ… / ሰው ስጡኝ…' (ቁ 8፣10)

እስራኤል - ግዙፉን ማን ሊዋጋው ነው? እስራኤልን ማን ሊያድን ነው?

የጦርነቱ አውድ - ቁ 1-3

አስፈሪው ጠላት - ቁ 4-9

የሚፈሩ የእግዚአብሔር ሰዎች - ቁ 11.

ያ ሰው ወዴት ነው?

ከዘፍ 3:15 ጀምሮ አለም ሲጠይቅ የነበረው ጥያቄ ነው። የእባቡን ጭንቅላት ማን ይቀጠቅጣል? ከ 1 ሳሙ 16 ጀምሮ - የተቀባው ንጉስ ብቃቱን እንዴት ያሳያል? የእግዚአብሔርን መንግሥት በሕዝቡ ላይ እንደገና የሚያጸናው እንዴት ነው?

1. እግዚአብሔር የመረጠው ሰው። ዳዊትን ማንም ሰው ሊመርጠው አይችልም።
2. ታናሽ ወንድ ልጅ ነበር፣ አስፈላጊ ያልሆነ ልጅ ነበር - ቁ 12
3. የእግዚአብሔር ንጉሥ የሚሆን የተቀባ ልጅ - 16:13

4. ከአባቱ የተላከ ልጅ ነበር - ቁ 17፣18
5. ችግሩን የተገነዘበ ልጅ ነበር - ቁ 23
6. ለአምላኩ ክብር የሚጨነቅ ልጅ ነበር - ቁ 26
7. በወንድሞቹ የሚዘባበትና በሃሰት የሚከሰስ ነበር - ቁ28-29. ዮሐንስ 1:10፣ 11 ኤልያብ የዳዊትን ልብ በተመለከተ ያደረገው ግምገማ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነፃፀር - ቁ 28፣ 1 ሳሙ. 13:4፣ 16:7።
8. ብቁ ልጅ ነበር - ቁ 34-36
9. አማኝ ልጅ ነበር - ቁ 37
10. የአለምን የጦር መሳሪያዎች የማይጠቀም ልጅ ነበር - ቁ 38-39. (ያመሳክሩ) ፈተናዎች

11. የራሱን መሳሪያ የሚመርጥ ነበር- ቁ 40
12. ጠላትን የሚጋፈጥ ነበር - ቁ 41-44
13. በጌታ ስም የሚመጣ ነበር - ቁ 45፣46
14. በሰው ድካም ነገር ግን በመለኮታዊ ጥንካሬን ያሸነፈ ነበር - መስቀል ሰይጣን የተጣለበት ነው - ቁ 48-51; ዮሐንስ 12:31; 1 ዮሐንስ 3:8፣ ዕብ 2:14፣15
15. እስራኤል ድል አድራጊ የሆነበት ምክንያቱ ልጁ ድል አድራጊ ስለሆነ ነው - በእርሱ ድል ደስ ይላቸዋል - 52-54፣ 1ኛ ቆሮ 15:57፣ ሮሜ 7:24፣25
16. ሰውየው ማነው? የማን ልጅ ነው… ወንድ ልጅ… (ቁ 58)

ማጠቃለያ፦ ክርስቶስ ክፉውን አጥፍቶ የእግዚአብሔርን መንግሥት መልሷል። በዚህ ትደሰታላችሁ? እናንተ ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ናችሁ? ድናችኋል?

ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ቁጥር ወደ 4 ወይም 5 እቀንሳለሁ - ይህንንም የማደርገው ጠንካራ የሆኑትን ነጥቦች በመምረጥ፣ አንዳንዶቹን በመተውና ሌሎችን በማዋሃድ ነው።

እያተከታተላችሁኝ ይህንን በአድርጉ። ጎልያድ? - በሰይጣንና በኃጢአት ላይ አተኩሩ። በመጀመሪያ ከእግር ድልድይ ወደ መንገድ ሂዱ፣ ከዚያም በድልድዩ ስር ወደሚገኘው ነጥብ ኑ - ወዲያውኑ ወደ ሥነ ምግባራዊ ተዛምዱ አትሂዱ።
ከክርስቶስ ጋር ንጽጽርን መሳል ያስፈልጋል ነገር ግን ልዩነቶቹንም ማሳየት አስፈላጊ ነው - ዳዊት ክርስቶስ አይደለም እናም ንጽጽሮቹ ፍጹም አንድ አይነት አይደሉም!

*መዝሙረ ዳዊት* **102**

ብዙ ጊዜ (ከ6፣ 32፣ 38፣ 51፣ 130 እና 143 ጋር) አብሮ የሃዘን መዝሙር ተብሎ ይጠራል ነገር ግን ምንም አይነት የኃጢአት ኑዛዜ የለም። በቁ 10 ላይ መዝሙረኛው መከራው በእግዚአብሔር ቁጣ የተነሣ እንደሆነ ይገነዘባል። መዝሙረኛው እግዚአብሔር ፊቱን እንዳይሰውርበት ይጠይቃል (ቁ 2)፣ ደካማነቱንና ጭንቀቱን ይገልፃል (ቁ 3-11)፣ ከዚያም ሀሳቡን ወደ እግዚአብሔር ያነሳና "እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን…" (ቁ 12) የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ምሕረት ያሰላስላል (እስከ ቁ 17)። መመዝገብ ያለበት መልእክት የሚከተለው

ነው፡ ለሕዝቡ መቃተት የእግዚአብሔር ርኅራኄና እርሱን እንዲያመልኩ መልቀቁ (18-22)። በመጨረሻው ክፍል ቀደም ሲል የተናገረውን ጠቅለል አድርጎ ገልጿል - "ብርታቱን መንገድ ላይ ቀጨው" (ቁ 23) በማለት አዝኗል።

ቁጥር 25-27 የእግዚአብሔርን ዘላለማዊና የማይለወጥ ባሕሪ ይገልፃል እናም ይህ በዕብራውያን 1፡10 የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ለማረጋገጥ ተጠቅሷል። ለዕብራውያን ጸሐፊ ይህ ማለት እግዚአብሔር መሲህ ለሆነው ልጁ የተናገራቸው ናቸው ማለት ነው (ዕብ. 1፡8 ተመልከት)። መሲሑ በፍጥረቱና በአገዛዙ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነው። ነገር ግን መሲሑ የእግዚአብሔርን ቁጣ ተሸክሞ መከራን ተቀብሏል ነገር ግን በራሱ ኃጢአት ምክንያት አይደለም። ታዲያ መዝሙሩ በሙሉ የሚያመለክተው እርሱን አይደለምን? መከራው ከሕዝቡ ጋር የተቆራኘው የእግዚአብሔር አገልጋይ አይደለምን? ከክርስትና ዘመን በፊት የተተረጎመው የግሪክ የመዝሙር ትርጉም መዝሙሩን ከመሲሑ ጋር አዛምዶ ይተረጉመዋል ስለዚህም ቁ 24ለ-28 እግዚአብሔር መሲሑን እየተናገረ ነው፣ ከ1-11 ያለው መዝሙር የመሲሑን መከራ ይናገራል፣ እንዲሁም ደግሞ የመዝሙር 12-22፣ 28 ስለ እርሱ ክብርና ዓለም አቀፍ ግዛት ያወራል።

ኤርምያስ **26**

የእግዚአብሔር አገልጋዮች መከራ በአዲስ ኪዳን ተዘግቧል፡ ለምሳሌ እስጢፋኖስ (ሥራ 6፡8-8፡1)፣ ጳውሎስ (16:20-24፤ 21:27-25:26)፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል። ከኤርምያስ መከራ ጋር ተመሳሳይነት ለማግኘት አስቸጋሪ አይደለም። በመጀመሪያ የኤርምያስ ሕይወት ለተወሰነ ጊዜና ከተለያዩ አካላት በመሚቃጣ መከራ ደርሶበታል (11፡21፤ 18፡23) የኢየሱስ ሕይወትም እንዲሁ ነበር (ማር 2፡6፤ ሉቃስ 11፡53፡54፤ ሉቃ 48)። ሁለተኛ ሙሉ በሙሉ ኢፍትሐዊ ነበር። ኤርምያስ የጌታን ቃል በታማኝነት በመናገሩ ለፍርድ ቀርቦ ነበር። ጌታ ኢየሱስም የአባቱን ፈቃድ በማድረጉ ለፍርድ ቀርቦ ነበር፤ በእርሱ ላይ ከተመሰረተው ክስ ሁሉ ንጹህ ነበር (ማቴ 26፡59-61)። ከኤርምያስ በተለየ መልኩ ጌታ በሁሉም ረገድ ፍጹም ጻድቅ ነበር። ሦስተኛ የሃይማኖት ባለ ሥልጣናት ከሳሾች ነበሩ (ማቴ 26፡57-68) እናም እርሱ እግዚአብሔርን ተሳድቧል ብለው ከሰሱት (26፡65)፤ ኤርምያስም ሞት የሚገባው ሐሰተኛ ነቢይ ወይም እግዚአብሔርን ተሳዳቢ ነው ተብሎ በተሳካ ሁኔታ

ተከሷል። አራተኛ ለጲላጦስ እንደ ገቸ ይግባኝ ለማለት (ቢያንስ በሕዝብ ባለስልጣን ፊት) ሲባል ክሱ የቀረበው እንደ ሐይማኖታዊ ክስ ሳይሆን እንደ ሕዝባዊ ክስ ሆኖ ነው (ሉቃ 23፡2፣5)። አምስተኛ ኢየሱስ

ለባለ ሥልጣናት ተላልፏል ወይም ተላልፎ ተሰጥቷል (ሉቃ 9:44፤ ማቴ 26:2፤ ደግሞም በጲላጦስ ዮሐ 19:11፣16)፤ ኤርምያስ "መልካምና ተገቢ መስሎ የሚታያችሁን ሁሉ" ታደርጉብኝ ዘንድ እነሆ "በእጃችሁ ነኝ" በማለት ተናግሯል። በእነዚህ በእያንዳንዱ ክስተት ላይ ያለው ተከሳሽ ምንም ማድረግ የማይችል ሆኖ ሳይሆን ተገዢ ሆኖ ነው "ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት" ሆኖ ተወስዷል (ኤር 11:19)። በመጨረሻ ላይ ልጁን ወይም አገልጋዮቹን አሳልፎ የሚሰጠው እግዚአብሔር መሆኑ የማይታመን ነው (ሐዋ 2:22፣23)። እነርሱ በመጨረሻም ሕይወታቸው በእግዚአብሔር እጅ እንዳለ ያውቃሉ (1 ጴጥ 2:21-23)። ስድስተኛ ወንጀለኞቹ ተከሳሹን ለመግደል ቀጣዩን እርምጃ ከወሰዱ ለሞት አደጋ ይጋለጣሉ (ቁጥር 15)። ለምሳሌ የኢየሱስን ጉዳይ ስንመለከት የአይሁድ ሕዝብ በራሳቸው ላይ አስፈሪ እርግማን ጠርተዋል (ማቴ 27:25)፤ የጲላጦስ ሚስት ሕልም አየችና ጲላጦስ ከዚያ "ንጹሕ ሰው" ጋር የተያያዘ ምንም አይነት ንክኪ እንዳይኖረው አስጠነቀቀችው (ማቴ 27:19)፤ ኢየሱስ በሰማይ ደመና የሚመጣ የሰው ልጅ ነው በማለት ስለ ፍርድ ያስጠነቅቃል (ማቴ 26:64) እናም በመስቀል መንገድ ላይ ሆኖ በኢየሩሳሌም ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ያስጠነቅቃል (ሉቃ 23:28-31)። ሰባተኛ ሁለቱም ሰዎች በሕዝብ ፍርድ ቤት ንፁህ ናቸው ተብሎ ተፈርዶላቸዋል። ጲላጦስ ሦስት ጊዜ ኢየሱስን ንጹሕ እንደ ሆነ ተናግሯል (ሉቃ 23:4፤ 14-16፤ 22) ያም ብቻ ሳይሆን ከጉዳዩ ንፅህ ነኝ ብሎ እጁን ታጥቧል (ማቴ 27:24)። ነገር ግን ይህን በማድረግ በሃይማኖት መሪዎቹ ተታልለው እዚህ ደረሱት ሰዎች ተይዞ ይሰቀል ዘንድ ተጎጂውን አሳልፎ ይሰጣል (ማቴ 27:20-23)። ቀጥሎ እንደምናየው ኤርምያስ በባለሥልጣናቱና በሕዝቡ ዘንድ ንጹሕ ነው ቢባልም በእርሱ ጉዳይ ግን ጥበቃ አለ - የሃይማኖት መሪዎች፣ ካህናትና ነቢያት የፈለጉትን ማድረግ አልቻሉም። እዚህ ላይ ኤርምያስ በእርግጥ የክርስቶስ ምሳሌ ነው፤ የሚበልጥ የጽድቅ ሕይወት ምሳሌ ጠቋሚ፣ ይበልጥ የሚያስፈራ ሥቃይ ጠቋሚ፣ ይበልጥ ውጤታማ የሆነ መከራ. "ወደ እግዚአብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ፣ ጻድቅ የሆነው እርሱ ስለ ዐመፀኞች ሞተ" (1 ጴጥ 3:18) ጠቋሚ ነው።

የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች

ክርስቶስን ከአዲስ ኪዳን መስበክ መቻል አለብን ነገር ግን ብዙ ስብከቶች ወደ ወንጌል ሳይደርሱ የሥነ ምግባር ትምህርቶች ብቻ ሆነው ይቀራሉ። እራሳችንን ማትጋት መቻል አለብን፡ ኢየሱስን እንደ ክርስቶስ እየሰበኩ ነውን? ወይም እንደ ሥነ ምግባር አስተማሪ ወይም ምሳሌ ነው እየሰበኩት ያለሁት? ""ጌታው፤ እባክህን፣ ኢየሱስን ለማየት እንፈልጋለን" (ዮሐ 12:21) የሚለው ጥያቄ ክርስቶስን አዲስ ኪዳንን ጨምሮ ከቅዱሳት

መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር የተስፋዎች ፍጻሜና የቤዛነት ሥራው የተጠናቀቀበት መሆኑን በመስበክ መመለስ ያለበት ጥያቄ

ነው። ክርስቶስን የኃጢአተኞች አዳኝ መሆኑን ለማቅረብ ትክክለኛ መንገዶችን ፈልጉ። ለክርስቲያኖች በምትሰብክበት ጊዜም ቢሆን በተለያዩ ቦታዎች ወንጌልን ማካተት አለብን። ያለ ወንጌል "የእግዚአብሔር ምክር ሁሉ" አልተሰበከም።

ክርስቶስን መስበክና ለጽሑፉ ዓላማ ታማኝ መሆን የምችለው እንዴት ነው? ብለን የምንጠይቅባቸውን ጥያቄዎች ሊመልሱ የሚችሉ ሁለት ምንባቦች መርጫለሁ። አንዳንዶች ይህን አንድምታ ብለው ሊጠሩት ይችላሉ - ከክርስቶስ ወይም ከሥራው ጋር በተጻፈ ጽሑፍ ውስጥ የሚታዩ ተመሳሳይነቶች ሕገ-ወጥ አተገባበር ሲሆን ይህም "ክርስቶስን በሁሉም ቦታ ለማየት" ባለና ከመጠን በላይ በሆነ ፍላጎት የሚመጣው ነው። ነገር ግን ይህ መርህ አእምሯችሁን ስለ ክርስቶስ ማንነት እና ስላደረገው ነገር ዋና እና ተቆጣጣሪ እውነቶች ላይ አኑሩ እንጂ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ወይም ተጓዳኝ ጉዳዮች አትቅረቡ የሚል ነው።

ሉቃስ **10:25-37**

ጠበቃው አንድ አስፈላጊ ጥያቄ ይጠይቃል "መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ላድርግ?" (ቁ 25፣ ሀብታም ወጣት ገዥ የጠየቀውን ያመሳክሩ 18:18)። ኢየሱስ ጠበቃው የሚያውቃቸውን ሁለት ታላላቅ ትእዛዛት በመንገር መለሰ። የሚያውቀውን መልስ እንዳገኘ ለመጠቆም ጠበቃው "ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማን ነው?" ሲል ጠየቀ። ኢየሱስ ለጋስነቱ የዘርና የሃይማኖት ጥላቻን ያሸነፈውንና ተስፋ አስቆራጭ በሆነ ሁኔታ ውስጥ የነበረውን (የሚገመተውን) አይሁዳዊ ለመርዳት ስለሞከረው ሳምራዊው ምሳሌ በመናገር መለሰ።

ነገሩን በዚህ እንተውዋለን? ባልንጀራህን ውደድ የሚለውን ሁለተኛውን ታላቅ ትእዛዝ እንዴት መፈጸም እንዳለብን የሚናገር ጉልህ መልዕክት ነው። መልሱ የሚመልሰው "ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማን ነው?" የሚለውን ጠበቃው የጠየቀውን ጥያቄ አይደለም ይልቁንም ልንማር የሚገባንን "ጎረቤት መሆን ማለት ምን ማለት ነው" የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል።

ነገር ግን ኢየሱስስ ምን ዓይነት ባልንጀራ ነበር? በትክክለኛው መንገድ ብለን መጠየቅ አንችልም? በሰይጣንና በኃጢያት መዳፍ ውስጥ ነበርን ልያውም ተደብድበን። በእግዚአብሔር ልጅ ፍቅር ላይ ምንም የይገባኛል ጥያቄ አልነበረንም። እርሱ እንደ ሌዋዊውና ካህኑ (ነገር ግን ከእነርሱ በተቃራኒ በሙሉ የጽድቅ ውሳኔ) ሊያልፈን ይችል ነበር። "ነገር ግን ሥጋን በመንሳት እኛ ወደነበርንበት ሊመጣ መረጠ፤ የሰው ልጆች በመስቀል

©ብራና ጎስፐል ፎከስ ሚኒስትሪ *2022*

ላይ ሊሰቅሉት ቢያሳድዱትም ራሱ ዋጋ ከፍሎ አዳነን ደግሞም ለቤዛነታችንና ሊታለም ለማይችል ክብር ለሚሆን ፍጽምናችን

ዋጋውን አስቀድሞ ከፍሏል" (ዴቪድ ጉዲንግ፣ በሉቃስ መሠረት፣ አይቪፒ፣ 1987፣ ገጽ 204-05/ David Gooding, *According to Luke*, IVP, 1987, p 204-05)።

ፊልሞና

ጳውሎስ ለሸሸ ባሪያ ስላሳየውን ደግነትና ቤተ ክርስቲያን አዲስ ለዳነ ሰው ልትሰጥ ስለሚገባት ትክክለኛ ምላሽና ሌሎች ብዙ መልካም የሆኑ ተግባራዊ ትምህርቶችን ጨምራችሁ "የሚጠቅም" ስብከት መስበክ ትችላላችሁ ነገር ግን እዚህ ላይ መታየት ያለበት ሌላ ነገር አለ?

1. የማይጠቅም ባሪያ - አናሲሞስ።
2. የተለወጠና አሁን ያሉት ሁሉም ግንኙነቶቹ ሁሉ "በጌታ" የሆኑ - ቁ 16። የከፋው ባርነቱ የኃጢአት ሥራ ነበር፤ አሁን ከዚያ ነጻ ወጥቷል።
3. ጳውሎስ አናሲሞስን ደግፎ የቆመ ነው። እንደ ጳውሎስ አድርጎ አናሲሞስን እንዲቀበለው ፊልሞናን ተማጸነ - ቁ 17. በሌላ አነጋገር ጳውሎስ ፊልሞና እርሱን እንደሚመለከተው አድረጎ አናሲሞስን እንዲመለከተው ይፈልጋል። ስለዚህ ልክ እኛ የጳውሎስ እንደምንመለከተው አይነት አናሲሞስ ከበደለው ከጌታው ከፊሊሞና ሞቅ ያለ አቀባበል ይደረግለታል ማለት ነው። ስለዚህ ክርስቶስ ስለ እኛ በአብ ፊት ቆሟል። እርሱ ልክ እንደ እኛ ማለትም እንደ እናንነተና እንደ እኔ አድርጎ ያየን ዘንድ አብን ይጠይቃል። ስለዚህ ከበደልነው ከእርሱ ሞቅ ያለ አቀባበል እናገኛለን።
4. ጳውሎስ ከፊልሞና ጋር ባለውን ግንኙነት የእርሱን ጽድቅ ሊያመለክት ይችል ነበር የእርሱን ፍቅር፣ የእርሱን ጓደኝነትና እነዚህን ነገሮች በአናሲሞስ ክፋት፣ ፍቅር ማጣት፣ ግንኙነት ማበላሸት ፈንታ ፈንታ እንዲያስቀምጥ ይነግረዋል።
5. ጳውሎስ የአናሲሞስን ዕዳ ለመክፈል ፈቃደኛ ነው - ቁ 18። ክርስቶስ 'ዋስታችን' እንደ ሆነና የእኛን እዳ እንደ ተቀበለ ሁሉ ጳውሎስም የባሪያውን ዕዳ ይቀበላል (ኢሳ 53፡5፣6፤ ቆላ 2፡14)።
6. በክርስቶስ በአብ ዘንድ እንደ ክርስቶስ ታይተን ተወድደናል (ዮሐ 17፡23)።
7. ቁልፉ መታወቂያ ነው - ክርስቶስ ከእኛ ጋር አንድ ሆኗል፣ እርሱ ለእኛ ሰው ሆነ፣ ስለዚህ ከእኛ ጋር አንድ ሆኖ በመገናኘቱ ታላቅ ልውውጥ ማድረግ ይችላል። እርሱ ኃጢያታችንን ወሰደ እኛ ደግሞ ጽድቁ ተቀበልን (2 ቆሮ 5፡21)። በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሆናችኋል እግዚአብሔርም በእርሱ ያያችኋል። ስለዚህ በክርስቶስ ዕዳችሁ በእርሱ ተከፍሏል፣ በክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር

ታርቃችኋል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሆናችኋል፣ በክርስቶስ ከክርስቶስ ጋር የእግዚአብሔር የጋራ ወራሽ ናችሁ።

እነዚህ ነገሮች ጳውሎስ ለአናሲሞስ በመቆሙና ዕዳውን ለመክፈል ፈቃደኛ በመሆኑ ተጠቁመዋል። ወንጌልን ከፊልሞና መስበክ ትችላላችሁ።

ሞስቲን ሮበርትስ፣

ግንቦት 16 ቀን 2022

©ብራና ጎስፕል ፎከስ ሚኒስትሪ ***2022***